# የብልፅግና ማኒፌስቶ

## ሕብረ ብሔራዊ ወንድማማችነት ለጋራ ብልፅግና

የካቲት /2013 ዓ.ም
ድሬደዋ

## የብልፅግና ርዕይ

### ኢትዮጵያን አፍሪካዊት የብልጽግና ተምሳት ማድረግ

የምናልመው የኢትዪጵያ ብልጽግና ቁሳዊ፣ሰብአዊ እና የማይዳሰሱ ማህበራዊ ሀብቶቻችንን አቀናጅተን በማነጽ የምንፈጥረው አቅም፤ ያም አቅም በተራው የሚፈጠረው ጥሪትና የሚገነባው ስራዓት፣ የሕዝቦቻችንን ሁለንተናዊ መሻት በማሟላት የሚፈጠሩት ተድላና እርካታን የያዙ ሁለመናዊ ብልጽግና ነው፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝቦች መገለጫው የሆነውን ሕብረ ብሔራዊ ማንነትና ብዝሃ እምነት ዘው፣ ቱባ ባህሎቻቸው ተከብረውና እንዲያብቡ ተደርገው፣ እንደአንድ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ከተንቀሳቀሱ፣ አሁን ካለው የፖለቲካና የኢኮኖሚ ችግር ተላቀው እንደበለፀጉት ሃገሮች በተድላና በእርካታ በሰላም የማኖሩበት ምንም ምክንያት የለም ብለን እናምናለን፡፡

በፖለቲካው የፖለቲካችን ዋነኛ ዓላማ ለሁሉም ዜጎችዋ የምትስማማ፣ ሁሉንም ኢትዮጵያዊያን የምትመስል፣ የበለፀገች፣ የብሔሮችን መብት ከግለሰብ መብቶች ጋር አጣጥማ የምታስጠብቅ፣ ጠንካራ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ መገንባት ነው፡፡

ይህን ዓላማ ለማሳካት የምንከተለው መንገድ፡-

- እስከኣሬ እነ ሀገር ባመዘገብናው ድሎች ላይ መገንባት
- የቀደመውን ትሩፋትና ስኬት ማስጠበቅና ማጠናከር፣
- ከቀደመው ስሕተቶች መማር መታረም፣
- በትናንት ውስጥ መንዳምእዳም፣ በቀደመው የታሪክ ምዕራፍ ውስጥ ድልም ሽንፈትም እንደነበረ መገንዘብ፣
- በጎውን በማስቀጠልና በማሳደግ፣ ከፉውን ማረምና አለመድገም ናቸው፡፡

በኢኮኖሚው ሁሉም ኢትዪጵያዊ አቅሙ ፈቀደም አልፈቀደም፣ ለመኖር መሰረታዊ የሆኑትን ነገሮች ማግኘት እንዳለበት ብልጽግና ያምናል፡፡ ዜጎች ተመጣጣኝ ምግብ መጠለያ፣ ንፁህ የመጠጥ ውኃ፣ መሰረታዊ የጤናና ተምህርት አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን አለባቸው ብለን እናምናለን፡፡ ዜጎች እምቅ ችሎታቸውን በመጠቀም ሀብትን በፍትሐዊነት ለመፍጠርና ለመቋደስ የሚያስችሏቸውን የትምህርት፣ የጤና እና ሌሎች አገልግሎቶች በያሉበት በጥራት ሊደርሳቸው ይገባል ብለን እናምናለን፡፡ በተቸማሪም ዜጎች እነዚህን አገልግሎቶችን ለማግኘት በኢኮኖሚያዊ፣ ማህበረሰባዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ያለምንም ተጽዕኖ በእኩልነትና በፍትሃዊነት ተሳታፊና ተጠቃሚ መሆን ይገባቸዋል ብለን በፅኑ እናምናለን፡፡ ይህንንም እምነታችንን የሚያሳካ እና የመላውን ኢትዪጵያ ሕዝቦች የዘመናት መሻትን የሚያሟላ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማሕበራዊ እቅድ አዘጋጅተናል፡፡ ከዚህ በታች በማኒፌስቶ መልክ የቀረበውን ሀገራዊ ብልጽግና ራዕያችንን የሚጋሩ ከሆነ፣ ድምፆን ለብልጽግና ፓርቲ በመስጠት የኢትዮጵያን የብልጽግና ጉዞ እንዲቀላቀሉ በአክብሮት ተጋብዘዋል፡፡

# ምዕራፍ አንድ
# ህብረ ብሔራዊ ፌደራላዊ ሥርዓት ላይ የተመሰረተ የህገረ መንግስት ግንባታ

## 1.1 ተቋማዊ መሰረት ያለው የዴሞክራሲ ሥርዓት

1. ፓርቲያችን የህዝብ ሉአላዊነት ተከብሮ የመንግስት ስልጣን በህዝብ ይሁንታና ውክልና በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ሊገኝ ይገባል ብሎ ያምናል። ፓርቲያችን ዴሞክራሲ የህዝብ ወኪሎች ከሚመረጡበት የምርጫ ሂደት አልፎ በሂደቱና ውጤቱም የዜጎች እኩልነትና ነፃነት የሚጎለብትበት መሆኑን ያምናል። በተጨማሪም እንደ ኢትዮጲያ ብዝሃነት የሚንፀባረቅባቸው ሀገራት በፉክክር ላይ ብቻ የተመሰረተ ሳይሆን ትብብርንም የሚያካትት የዴሞክራሲ ሥርዓት ተግባራዊ መሆን እንዳለበት ፓርቲያችን ያምናል። ስለዚህ ፓርቲያችን በትብብር ላይ የተመሰረተ፣ አካታች ዴሞክራሲያዊ ሥርአት እንዲገነባ ይሰራል።
2. የመንግስት አካላት ተጠያቂነት ማረጋገጥ የዴሞክራሲ ግንባታችን ቁልፍ ጉዳይ መሆን እንዳለበት ፓርቲያችን ያምናል። ፓርቲያችን ማንኛውም ፖለቲካዊ፣ርዕዮተ-ዓለማዊ፣ህጋዊ ወይም ሌሎች እንቅስቃሴዎች ሁሉ ህገ-መንግስትን የተከተሉ እንዲሆን ያደርጋል።
3. የህግ አውጭው፣የሕግ አስፈጻሚው እና የሕግ ተርጓሚው የስልጣን ክፍፍል በአግባቡ ተፈፃሚ እንዲሆንና የእርስ በርስ ቁጥጥርና ሚዛን እንዲጠናከር ሕግ አውጭውን የሚያጠናክሩና የዳኝነት አስተዳደሩን የሚያጎለበቱ አሰራሮች ይዘረጋሉ።
4. ፓርቲያችን የሀገራችን የዴሞክራሲ ሥርዓት የግለሰብ መብቶችንና የቡድን መብቶችን ሳያበላልጥ የሚያስከብርና ሁለቱንም የመብት ዓይነቶች ለማስከበር በየባሕሪያቸው ልክ የተቀየሰ አቅጣጫን የሚከተል ይሆናል። በመሆኑም ግለሰባዊና ቡድናዊ ጭቆናን በተናጥል ሳይሆን ለሁሉቱም አንፃራዊ ትኩረት በመስጠት ለመብቶቹ መከበር የሚሰራ ይሆናል።
5. የሲቪል አስተዳደር፣መከላከያ፣ዳኝነት፣ፖሊስ፣ ከፖለቲካ ነፃ ሆነው እንዲደራጁ፤ሥራዎች ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለባቸው እንዲሆኑ

5. የሲቪል አስተዳደር፣መከላከያ፣ዳኝነት፣ፖሊስ፣ ከፖለቲካ ነፃ ሆነው እንዲደራጁ፤ሥራዎች ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለባቸው እንዲሆኑ ለማስቻልና ስርቆትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ልዩ ልዩ አሰራሮች ይዘረጋሉ፡፡

6. የዜጎች መሠረታዊ መብቶች መከበርን የሚያረግግጥ የቁጥጥር ሥርአት መዘርጋት የፓርቲያችን አንዱ የትኩረት መስክ ነው፡፡ ሀሳብን የመግለጽ፣የመሰብሰብና የመደራጀት፣በእኩልና ያለ አድልኦ የመታየት፣የግል ሚስጥርን በዘፈቀደ ያለመገፈፍ፣የፈለጉትን እምነት የመከተል እና የመሳሰሉት መሰረታዊ የሰው ልጅ መብቶች መከበራቸውን የሚያረጋግጥ የክትትል ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

7. ፓርቲያችን ነፃ እና ገለልተኛ ሚዲያዎች እንዲጠናከሩ እና ለህዝቦች አብሮነት እና ወንድማማችነት መዳበር የሚሰሩ፣ከፖለቲካ ተፅዕኖ ነፃ ሆነው እንዲንቀሳቀሱ የህግ ከለላ የሚደረግላቸው ሲሆን ሚዲያው የሶስተኛው መንግስትነት ሚናውን እንዲወጣ በቁርጠኝነት ይሰራል፡፡

8. በሕግ ቁጥጥር ስር ያሉ ሰዎች መብታቸው ተከብሮና ሰብዓዊ ይዞታቸው ተጠብቆ እንዲቆይ የማረፊያና ማረሚያ ቤቶች የቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

9. የሰብአዊ መብት ተቋማት የቁጥጥርና የጥናት አቅማቸው እንዲያድግና ከማንኛውም ተፅዕኖ ነፃ ሆነው መስራት ይችሉ ዘንድ አቅማቸው እንዲጎለብትና የአስተዳደር ነፃነት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

10.የህግ የበላይነትና ፍትህን ለማስፋን የህግ አሰከባሪና የፍትህ ተቋማትን ማጠናከርና የሕግ ጥራትን ማረጋገጥ ከፓርቲያችን የትኩረት አቅጣጫዎች አንዱ ነው፡፡ የፍትሕ ተቋማትን ብቃትና ነፃነት ለማጠናከር ፓርቲያችን ተከታታይነት ያለው የሪፎርም እና የአቅም ግንባታ ስራ ይሰራል፡፡ በነዚህ ተቋማት ላይ የህዝብ አመኔታ እንዲጨምርና አስተማማኝ ደረጃ ላይ እንዲደርስ ፓርቲያችን ይሰራል፡፡

11. ወንጀል መከላከል ስትራቴጂ፣ፕሮግራምና መርሃግብሮች በመንደፍና በመተግበር፤ወንጀልና የወንጀል ስጋት አካባቢዎችን፣የወንጀል አይነትና ወንጀል ፈፃሚዎችን መለየት የሚያስችል ስርዐት በመዘርጋትና በመተግበር፤ህብረተሰቡን በተደራጀ መልኩ በማሳተፍ፤የወንጀል መከላከል በሰው ሀይል እውቀት፣በቴክኖሎጂ፣ልዩ ክህሎት በሚፈልጉ ዘዴዎች በማጠናከር፣የወንጀል የጥቆማ፣ክስና አቤቱታ አቀባበልና ምዝገባ ስርአቱ ቀላልና ዘመናዊ በማድረግ፤ የሳይንሳዊ፣የፎረንሲክና ሕክምና ምርመራ አቅምን በማጠናከርና በማስፋት ወንጀልንና የወንጀል ስጋትን ለመቀነስ ፓርቲያችን ይሰራል፡፡

12. ፓርቲያችን ቀድሞ በህግ አወጣጥ ረገድ የታዩ ዝንፈቶችን በማረም የሚወጡ ህጎች ግልጽ፣የውስጥ መናበብ ያላቸው፣ከህገ-መንግስቱ ጋር የማይጣረሱ፣እንዲሁም የዜጎችን መሠረታዊ መብቶች የማይጋፉ እንዲሆኑ በከፍተኛ ጥናትና የሕዝብ ተሳትፎ በጥንቃቄ እንዲወጡ ይደረጋል፡፡

13.ፓርቲያችን የህዝብ አስተዳደር ወይም ሲቪል ሰርቪስ ቅልጥፍናና ብቃት በየጊዜው እየጨመረ እንዲሄድ ያልተማከለ እና የተቋማቱን ባህሪያት ያገናዘበ፣በጥናትና በእውቀት የሚመራ የለውጥ መርሃ ግብር በየተቋማቱ እንዲተገበር በማድረግ በመንግስት ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ዜጎች ካላቸው ዕርካታና መተማመን እንዲጨምር በቁርጠኝነት እንሰራለን፡፡ በተጨማሪም ፓርቲያችን ጠንካራና ዘመን ተሻጋሪ የሆኑ ተቋማትን ለመገንባት በልዩ ትኩረትና ከፍተኛ ትጋት እና ቁርጠኝነት ይንቀሳቀሳል፡፡

14.ፓርቲያችን ዴሞክራሲ በትምህርት፣በጤና፣ በመሠረተ ልማት ግንባታ በመታጀብ አሰላሳይ፣ሞጋችና ፈጣሪ ኀብረተሰብ በመፍጠር ረገድ አስተዋፅዖ ሊኖረው ይገባል ብሎ ያምናል፡፡ በመሆኑም የምንገነባው ዴሞክራሲ ተቋማዊ መሠረት ያለው እንዲሆንና የዴሞክራሲ እሴቶችም ወደ ባህልነት ደረጃ እንዲያድጉ ፓርቲያችን ይሰራል፡፡

15.በሰላም አብሮ የመኖር፣የመረዳዳት፣የመተሳሰብ የዘለቁ ባህሎችና እሴቶች እንዲዳብሩ በማድረግ አወንታዊ ሠላም በአገራችን እንዲሰፍን ይደረጋል፡፡ የዜጎችን ሠላም እና ደህንነት በዘላቂነት እንዲረጋገጥ ከመደበኛ ህግ ማስከበር በተጨማሪ አገራዊ እሴቶቻችንንና ሀገር በቀል እውቀቶችን ለሰላም ግንባታ እንዲውሉ እንሰራለን፡፡

ማህበራዊ ሀብቶችና እሴቶቻችን በመጠበቅ በቡድኖች እና ማህበረሰቦች መካከል ያለው ማህበራዊ ትስስር እና አብሮነት እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡ በአዎንትዊ ሰላም ዙሪያ ለዜጎች፣ የመንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ግንዛቤ መፍጠርና አበርክቶዋቸው እንዲያድግ የሚያግዙ አደረጃጀቶችን መፍጠርና የማጠናከር ስራዎች በስፋት እንሰራለን፡፡

16. የህግ ማስከበር አቅምን በማሳደግ የህግ የበላይነትን በተሟላ መልኩ እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡ በየደረጃው የሚገኝ የህግ ማስከበር ተቋማት ዜጋ ተኮር ህግ የማስከበርና የማክበር እንዲሁም ለዜጎች ሰብዓዊ መብት መከበር ትኩረት በመስጠት ዜጎች በፖሊስ እና በጸጥታ ተቋማት ላይ ያላቸው እምነት እንዲያድግ ይደርጋል፡፡ፖሊስና የጸጥታ ተቋማት የወንጀል ቁጥጥርና ክትትል ስራ አቅማቸው በማሳደግ እና ከጎረቤት አገራትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በጋራ በመስራት የተደራጁ ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎችን ማምከንና የመቆጣጠር ስራ ይጠናከራል፡፡ የወሳኝ ሁነቶች ምዝገባ ሽፋንን በማሳደግ እና ዓለም አቀፍ ደረጃውን ያሟላ ብሔራዊ መታወቂያ ካርድ ያላቸው ዜጎች ድርሻ እንዲያድግ እናደርጋለን፡፡

17. የፌደራል መንግስትና የክልል አስተዳደሮች ግንኙነቶችን ወደ ላቀ ትብብር እንዲሸጋገር እንሰራለን፡፡ የክልሎችና ማህበረሰቡን ፍላጎት መሠረት ያደረጉ የማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሰረት ልማቶችና ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን የፌደራል አካላትንና አጎራባች ክልሎችን በማስተባበርና በማቀናጀት የማሳደግ፣በፌደራልና ክልል እና በክልል መካከል የሚኖር ግንኙነትና ትብብርን ተቋማዊ ሆኖ በሰላም፣በህግ የበላይነትና በልማት ማዕቀፍ ውስጥ አንድ ኢኮኖሚና ፖለቲካ ማህበረሰብ እንዲፈጠር የሚያስችሉ ተግባራት በትኩረት ይከናወናል፡፡

18. በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች በየደረጃው የግጭት ቅደመ ማስጠንቀቂያና ፈጣን ምላሽ ሥርዓት በመዘርጋት፣በማደራጀትና በማብቃት አለመግባባቶች ወደ ግጭት ሳያድጉ እንዲፈቱ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

## 2. ብሔራዊ መግባባት እና እርቅን በመፍጠር ጠንካራ ሀገረ መንግስት መገንባት

1. ፓርቲያችን ብሔራዊ መግባባትን ለማዳበር በሚያደርገው እንቅስቃሴ ቅድሚያ ሰጥቶ ከሚሰራቸው ተግባራት አንዱ በሀገራችን የቂምና የጥላቻ ታሪክ ምዕራፍ እንዲዘጋ ማድረግ ነው፡፡ ይህን ለማሳካት ባህላዊና ዘመናዊ የእርቅ ሰላም ግንባታ አማራጮችን በመጠቀም እርቀ ሰላምን ለማምጣት በቁርጠኝነት ይሰራል፡፡ ለቀጣዩ ትውልድ ቂምና ቁርሾ ሳይሆን ሰላምና ወንድማማችነትን ለማውረስ የእርቀ ሰላም አማራጮችን ሁሉ ይጠቀማል፡፡
2. ፓርቲያችን በሔራዊ መግባባትን ለማምጣትን እጅግ መሰረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የሃሳብ መቀራረብ ለማምጣት የሚደረገው ጥረት ብሔራዊ መግባባት በሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ላይ ጥናት የሚያደርግ እና ሂደቱን የሚመራ ተቋም በማቋቋም በልዩ ትኩረት የሚሰራበት ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ለሀገረ መንግስታችን ቀጣይነት መሰረታዊ በሆኑ ብሔራዊ ጉዳዮች ላይ ብሔራዊ መግባባት ላይ ለመድረስ ሁሉንም የሀገራችን ህዝቦች አካታች በሆነ መልኩ የውይይት አውድ እንዲፈጠር ይሰራል፡፡
3. የሀገራችን ሊሂቃን ለብሔራዊ መግባባት የሚኖራቸው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ፓርቲያችን ይገነዘባል፡፡ በመሆኑም የፖለቲካ ሊሂቃን ለብሔራዊ መግባባት የሚጠበቅባቸው ሚና እንዲጫወቱ ይደረጋል፡፡ በጥናት ላይ የተመሰረተ ውይይት ወይም ተዋስዖን የሚያስቀድሙ ድርጅቶችን ከሁሉም የሀገራችን የፖለቲካ ሊሂቃን እና ፓርቲዎች ጋር በማድረግ የብሔራዊ መግባባትን ለማዳበር አበክሮ ይሰራል፡፡
4. የብሔራዊ መግባባት ሂደቱን የሚመሩ አስተባባሪዎች በብዙሃኑ ተቀባይነት ያላቸውና ገለልተኝነታቸው የተረጋገጠ እንዲሆን የሚደረግ ሲሆን፤የሚደረጉ ውይይቶችም ዘላቂነታቸው የተረጋገጠ እንዲሆን በልዩ ትኩረት ይሰራል፡፡ በተጨማሪም ለብሔራዊ መግባባቱ እንቅፋት የሚሆኑ አሰራሮች፣ህጎች እና መመሪያዎች ላይ ማስተካከያ ይደረጋል፡፡

5. ፓርቲያችን ሀገራዊ መግባባት ላይ ለመድረስ የግድ በሁሉም ጉዳዮች ላይ መስማማት አለብን ብሎ አይረዳም፡፡ ነገር ግና የትላንት በደሎች እና ቁርሾዎችን በህዝቦች መካከል የተተከሉ የጥላቻ ግንቦችን በሁሉን አቀፍ ይቅርታ መሻገር አለብን ብሎ ያምናል በመሆኑም ብሔራዊ መግባባቱም ከብሔራዊ ዕርቁ ጋር በጋራ እንዲከወን በልዩ ትኩረት የሚሰራበት ይሆናል፡፡

6.የብሔራዊ እርቅ ጉዳይ ከሌሎች ሀገራት ተሞክሮ በመነሳት በጥንቃቄ እና ሀገራዊ አንድነታችንን እና ብሔራዊ መግባባታችንን ሊያጠናክር በሚያስችል አደረጃጀት የሚመራ እና በወንድማማችነት ወደ ብልፅግና የምናመራበት እንዲሆን ይሰራል፡፡

## 1.3. በወንድማማችነት እሴት ላይ የቆመ ህብረ ብሔራዊ አንድነት መገንባት

1. ፓርቲያችን ትኩረት የሚያደርገውና ሊያሳካ የሚፈልገው ብዝሃነታችንን የሚቀበልና የሚደግፍ ሥርዓት መፍጠርና እና በዚያው ልክ ህብረ ብሔራዊ አንድነታችንን ጠንካራ የሚያደርግ ሥርዓት መገንባት ላይ ነው፡፡ ፓርቲያችን የፌደራል ሥርዓቱ ዋና ምሰሶ ብዝሃነትን ማስተናገድ መቻሉ ነው ብሎ ያምናል፤በመሆኑም ለብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ዕውቅና የሰጠ ፌደራላዊ ሥርዓት በመገንባት የብሔሮች መብት የተከበረበት እውነተኛ ህብረ-ብሔራዊት አገር እንድትሆን ይሠራል፡፡
2. ፓርቲያችን በኢትዮጵያ የወንድማማችነት እሴትን ለማጎልበት የመደመር መንገድን ይከተላል፡፡ የመደመር እሳቤዎችን አንድ በአንድ እየተገበሩ በመሄድም የወንድማማችነት መንፈስ ከተኛበት የሚቀሰቅስ ፓርቲ ነው፡፡ የብሔሮችን ጥያቄ ያከበደው የወንድማማችነት መቅለል ነው ብሎ ስለሚያምን፣የብሔሮችን ጥያቄ የሚፈታው በወንድማማችነት ማዕቀፍ ነው፡፡
3. ፓርቲያችን በሕብረ-ብሔራዊነት ታሪካዊና ነባራዊ በደሎችን የሚያድበሰብስ ነገር ግን መስተካከልና መታረም ያለባቸውን የተዛቡ፣ኢ-ፍትሃዊ ግንኙነቶች በማረም ህብረትና ወዳጅነት የሚያጠናክር እና ህብረ- ብሔራዊ አንድነት ብዙ ሆነን አንድ፣ አንድ ሆነንም ብዙ የምንሆንበት፣ለጋራ አላማና ግብ አብረን መቆም፣አብረን መስራት እንዳለብን፣ዕጣ ፈንታችን እጅጉን የተቆራኘ መሆኑን በመገንዘብ በመንድማማችነት በመደጋገፍ፣በመተጋገዝ እንዲጎለብት ይሰራል፡፡

4. በሀገራችን ለዘመናት የህዝቦች እኩልነት ጥያቄዎች በህዝቦ መራር መስዋትነት ህገ መንግስታዊ እውቅና እንዲያገኝ የተደረገ የብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች በህገ መንግስቱ የተቀመጡ መብቶች ያለ ምንም መሸራረፍ ተፈፃሚ እንዲሆን ፓርቲያችን ይሰራል፡፡

5. በህገ መንግስታችን የተቀመጡ መንግስታዊ አወቃቀር ተጠያቂነት፤የስልጣን ክፍፍል የራስ አስተዳደርና የጋራ አስተዳደር ጉዳዮች ህብረ ብሔራዊ አንድነታችንን በሚያጠናክሩ መልኩ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

6. የነፃነትና የእኩልነት ጉዳዮችን በአገራችን ያቀነቀኑ ፓርቲዎች ቢኖሩም፣ሁሉንም ጥያቄዎች ለመመለስ መሠረት የሚሆነውን የወንድማማችነት ጉዳይ ያቀነቀነ ፓርቲ ግን በአገራችን አልታየም፡፡ በመሆኑም ፖርቲያችን ለሀገራችን ህብረ ብሔራዊነት መዳበር የርዕዮት እስረኝነት ሳይሆን በወንድማማችነት አማካዩን መንገድ መከተል የሁሉም ህዝቦችን ጥያቄ እኩል ዕውቅና በመስጠት ተግባራዊ ምላሽ ለመስጠት የሚሰራ ይሆናል፡፡

7. ፓርቲያችን የወንድማማችነትን ጉዳይ ዓላማ አድርጎ በመንቀሳቀስና ዜጎችን በወንድማማችነት የሚያስልፍ ጎዳናን በመከተል ሕዝቦች በወንድማማችነት እንዲቆሙና የአንዱን ችግር አንዱ እንዲረዳ በማድረግ ነባር ችግሮችን በይቅርታ ጠንካራ ሀገረ መንግስት በህብረ ብሄራዊነት እና በወንድማማችነት ለመገንባት በብሔራዊ መግባባት የበለጸገች ህብረ ብሔራዊት ኢትዮጲያን በሁሉም ህዝቦች ተሳትፎ ለመገንባት ይሰራል፡፡

8. ፓርቲያችን በወንድማማችነት ተልዕኮ በአጋርነት ተፈርጀው ከመሐል ፖለቲካው የተገለሉ ሕዝቦቻችንን ወደ መሐል ፖለቲካው እንዲመጡና በአገራቸው ጉዳይ ላይ እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ በአገራችን ታሪክ ሁሉንም ብሔሮች በበቂ ሁኔታ በወንድማማችነት አሰባስቦ የሚታገል እውነተኛ ህብረ-ብሔራዊ ድርጅት ለመሆንም በቁርጠኝነት ይሰራል፡፡

### 1.4 ብዝሃ ልሳን የሆነ የፖለቲካ ማህበረሰብ መገንባት

1. ለተለያዩ የሀገራችን ቋንቋዎች እድገትና ለሀገራዊ የቋንቋ ፖሊሲ ሥርዓት የሚመች የቋንቋ አካዳሚና ጥናት እንዲሁም የፖሊሲ ማዕቀፍ እንዲኖር ይደረጋል።
2. ሕብረ ብሔራዊ ሀገር የመፍጠር ትልም እውን ለማድረግ ይረዳ ዘንድ የኢትዮጲያ ብዘሃነትን በሚገልፅ መልኩ 5 የሥራ ቋንቋ እንዲኖር ይደረጋል።
3. በኢትዮጲያ ውስጥ የሚገኙ ብሔሮች በቋንቋቸው እንዲጠቀሙና ከጊዜ ወደ ጊዜ ቋንቋው እየዳበረ እንዲመጣ ለማድረግ ተገቢ የሆነ እገዛ እና ድጋፍ ይደረጋል።

# ምዕራፍ ሁለት
# ከምግብ ዋስትና ጥያቄ የተሻገረ የዜጎችን የምርጫ አድማስ የሚያሰፋ የበለፀገ ኢኮኖሚ መገንባት

**የአምስት ዓመት የፓርቲያችን የበለፀገ ኢኮኖሚ የመገንባት ግቦች፤**

- ጥራት ያለው የኢኮኖሚ እድገትንና የጋራ ብልፅግናን የሚያረጋግጥ የኢትዮጲያ ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ ገበያ መር የኢኮኖሚ ሥርዓት መገንባት
- መዋቅራዊ የኢኮኖሚ ለውጥ የሚያረጋግጥ የብዝሃ ዘርፍ የልማት ስትራቴጂ መከተል
- አርሶ አደሩንና አርብቶ አደሩን ያማከለ ጠንካራና ዘላቂ የገጠር ልማት ማረጋገጥ
- የአረንጓዴ አሻራ ስራችንን በማጠናከር አረንጓዴ ኢኮኖሚ መገንባት
- የከተማውን ህብረተሰብ መሠረታዊ የልማት ጥያቄ የሚመልስ የከተሜነት ሥርዓት መገንባት
- የድህውን የኑሮ ሁኔታና ደረጃ ያገናዘበ የዋጋ መረጋጋት ማስፈን
- ጥራቱን የጠበቀ ፍትሃዊ የመሰረተ ልማት ሥርጭት ማረጋገጥ
- ለቀጣዩ ትውልድ ዕዳን የማያወርስ ዘላቂ የልማት ፋይናንስ ማረጋገጥ
- ዲጂታል ኢኮኖሚን ማሳለጥ የሚያስችል የቴክኖሎጂ አቅም መገንባት

የፓርቲያችን ኢኮኖሚያዊ ብልፅግና ጉዞ የዜጎችን ሁለንተናዊ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚጨምር ፍላጎትን የሚያሟላ ነው፡፡ ሌሎች ፍላጎቶች የሚወለዱት አንዱን ፍላጎት ከማሟላት ነው፡፡ በመሆኑም የህዝቦችን ዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚያዊ ፍላጎት በማሟላት ከትላንት የኑሮ ደረጃቸውን ወደ ተሻለ ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ማሸጋገር ነው፡፡ በዚህም የአሁኑ የአምስት አመት የብልፅግና ጉዟችን የህዝቡን አሁናዊ የኢኮኖሚ ፍላጎት በማሟላት ወደ ሌላ የፍላጎት ደረጃ የማሸጋገር እና ወደ ተሻለ የኑሮ ደረጃ የማድረስ ነው፡፡

ፓርቲያችን ዜጎችን በዛሬ ድህነት ውስጥ ሳይሆን ነገ በተሻለ ሁኔታ ፍላጎታቸው ተሟልቶላቸውና ጥራት ያለው ኑሮ እንዲኖሩ ማድረግ ተቀዳሚ ግቡ ነው፡፡ በተለይም በከፍተኛ ድህነት ውስጥ የሚኖረው ለብዙ ግዜያት በፍጆታው ላይ ምንም አይነት ለውጥ ያላሳየው ህዝባችንን በተለየ ሁኔታ ከድህነት ለማውጣት እንሰራለን፡፡ አጠቃላይ ድህነትን ከግማሽ በላይ ለመቀነስ መስራት የጉዟችን ተቀዳሚ መዳረሻ ነው፡፡ ይህም ዘርፈ ብዙ የኢኮኖሚ ፍላጎቶችን የማሟላት ግብ የብዙሃን የኢኮኖሚ ተዋንያንን ተሳትፎና መስተጋብር እንዲሁም ውጤታማ የሀብት አጠቃቀም ይጠይቃል፡፡ ሁሉም የሚሳተፉበት የብዙሃን ኢኮኖሚ የጋራ ብልፅግናን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በዚህም ፓርቲያችን የኢኮኖሚ ተዋንያን ተሳትፎ የሚጨምር እና ምርታማነት የሚያረጋግጥ ስራዎችን በአንድ በኩል በትኩረት ሲሰራ በሌላ በኩል የዜጎችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በትኩረት ይንቀሳቀሳል፡፡ ሀገራችን ኢትዮጲያን በመጪዎቹ አመታት አፍሪካዊ የብልፅግና ተምሳሌት ለማድረግ ሀገር በቀል ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲ ማሻሻዎችን መሰረት በማድረግ ሁለንተናዊ ብልፅግና ለማድረግ ይሰራል፡፡ ኢኮኖሚያዊ ብልፅግናችን ሰው ተኮር ሲሆን ለዚህም ሁሉም የልማት ስራዎችን በዜጎች ላይ ተጨባጭ ለውጥ እንዲመጡ በትኩረት ይሰራል፡፡

## 2.1 ጥራት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገትንና የጋራ ብልፅግናን የሚያረጋግጥ የኢትዮጲያን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘብ ገበያ መር የኢኮኖሚ ሥርዓት መገንባት

1. ፓርቲያችን በኢኮኖሚ ውስጥ የተከሰቱ የሚዛን ክፍተቶች በማስተካከል ጥራት ያለው እና በተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ ውስጥ ምርታማነትና ተወዳዳሪነትን በመፍጠር ኢኮኖሚውን በፍጥነት ለማሳደግ ይሰራል፡፡ ይህን ጥራትና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ለማስመዝገብ የግሉ ዘርፍ ሚናውን በአግባቡ እንዲጫወትና የላቀ ሚና እንዲኖረው ማድረግ ልዩ የትኩረት አቅጣጫ ሆኖ ይተገበራል፡፡ ሆኖም መንግስት የግሉ ዘርፍ ተወዳዳሪ እንዲሆን የተለያዩ ማበረታቻዎችን እና ለእድገት ወሳኝ የሆኑ የመሰረተ ልማት ግብአቶች በማቅረብ የኢኮኖሚ እድገቱ ፈጣን፣ ዘላቂ እና ጥራት ያለው እንዲሆን ጉልህ ሚና ይጫወታል፡፡ በመሆኑም የግል ዘርፉን በማጎልበት፣የመንግስትን ሚና ከግሉ ዘርፍ ጋር በማስተሳሰር ጥራት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገትን ማስመዝገብ የሚያስችል አካሄድን ይከተላል፡፡ በዚህም የኢኮኖሚ ከፍተኛ የማምረት አቅም ላይ ለመድረስ በአለም አቀፍ የንግድ ዕሴት ሰንሰለት ውስጥ በበቂ ደረጃ ለማሳተፍ በአጠቃላይ በኢኮኖሚ ደረጃ በተለይም የአምራች ዘርፎች ቅልጥፍናን በመጨመር እንዲሁም ብክነትን በማስወገድ ስትራቴጂዎችን ይተገበራል፡፡
2. ፓርቲያችን ምቹ የኢንቨስትመንት እና ንግድ ከባቢን በመፍጠር አዳዲስ ስራ ፈጣሪዎችን በንግድ ስራ ዑደት የሚያጋጥማቸውን አሳሪና ለጊዜ እና ለገንዘብ ብክነት የሚዳርጉ ህግጋትን እን ተቋማዊ አሰራሮችን በማሻሻል የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ ወሳኝ የስራ ፈጠራ፣የቴክኖሎጂ እና እውቀት ሽግግር ሚና እንዲኖራቸው ይሰራል፡፡

3.አምራቹን እና የንግድ ህብረተሰብ ከፀረ-ውድድር እና ተገቢ ካልሆነ የገበያ ተግባራት፣የንግዱን ማህበረሰብ በማንኛውም የሃገሪቱ ክፍሎች በነፃነት፣ከአድሎና ሌሎች ህጋዊ የንግድ እንቅስቃሴውን ከሚገድቡ ሁኔታዎች ነፃ ሆኖ እንዲሰራ የሚያስችሉ አስተዳደራዊና ህጋዊ ማዕቀፎች ይተገበራሉ፡፡

4.ፓርቲያችን ለኢንቨስትመንት መስፋፋት አስፈላጊ የሆኑ አስቻይ የመሰረተ ልማትና የሎጂስቲክ አገልግሎቶችን ለማስፋፋትና ለማዘመን ትኩረት ይሰጣል፡፡ በሎጅስቲክ ዘርፍ ያሉ ተቆጣጣሪ ተቋማትን፣አገልግሎት ሰጪዎችን፣አስመጪዎችና ላኪዎችን በማቀናጀት በዘርፉ ያለውን የመናበብ እና የቅንጅት ችግር በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስችል አጠቃላይ የሎጅስቲክስ አመራር እና አደረጃጀት ሥርዓት ተግባራዊ ከማድረግ ባሻገር የሎጅስቲክስ ስርዓቱ በቴክኖሎጂ የተደገፈና በሰለጠነ የሰው ሀይል የሚመራ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

5.ፓርቲያችን መንግስት በባለቤትነት በሚያስተዳድራቸው የንግድ ተቋማት የሚታየውን ደካማ ምርታማነት ለመቅረፍ በጥናት ላይ ተመስርቶ ተቋማቱ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ወደ ግል እንዲዘዋወሩ የማድረግ ስራ ይሰራል፡፡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች በግል ዕውቀት፣ቴክኖሎጂ እና ሃብት በመታገዝ አሁን ያለባቸውን የኮርፖሬት አስተዳደር አቅም ችግር በማቃለል ለኢኮኖሚ ዕድገት የተሻለ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ለማድረግ እንቅስቃሴ ያደርጋል፡፡ ከዚህ ቀደም ለመንግስት ብቻ የተተው ዘርፎችን የግል ባለሃብቱ በውድድር እንዲሳተፍ በማድረግ ዜጎች የተሻለ አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

## 2.2 መዋቅራዊ የኢኮኖሚ ለውጥ የሚያረጋግጥ የብዝሃ ዘርፍ የልማት ስትራቴጂ መከተል

1. ፓርቲያችን የእድገት ምንጫችን በማስፋት ሀገራችን ያላትን ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችል የእያንዳንዱ ዘርፍ ምርታማነት በማሳደግ መዋቅራዊ ሽግግርን ያረጋግጣል፡፡ በዚህም ሀገራችን የመልማት አቅም ባላት ሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች ትኩረት በመስጠት ማነቆዎችን በመቅረፍ እንዲሁም ዘርፎች በሚያስመዘግቡት በወጪ ንግድ አፈፃፀም እና በሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ ተመስርቶ ማበረታቻና ድጋፍ በመስጠት እድገትን ያስመዘግባል፡፡
2. በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ከውጭ የሚገቡ እንደ ስኳርና ዘይት ያሉ መሰረታዊ ሸቀጦችን በሀገር ውስጥ ምርት በመተካት፣ለነዚህ ሸቀጦች የሚወጣውን የውጭ ምንዛሬ በመቆጠብና ለሌሎች ቅድሚያ የተሰጠባቸው ዘርፎች እንዲውል በማድረግ እንዲሁም ከዘርፉ የሚገኝ የውጭ ምንዛሬ ከፍ በማድር ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ያለውን ድርሻ አሁን ካለበት በእጥፍ ለማሳደግ የሚያስችል ምርትና ምርታማነትን የሚያሳድግ በጥራት፣ቅልጥፍ እና ተወዳደሪነት የሚያረጋግጥበት አሠራር ይተገበራል፡፡ ይህም እንዲሆን በዘርፉ ነባር አምራች እንዲስትሪ የማምረት አቅም ማጎልበት፣ አዳዲስ ኢንቨስትመንት በብዛት፣በጥራት እና በዓይነት ከማስፋፋት ባሻገር የአምራች ኢንዱስትሪውን የእሴት ሰንሰለት፣ትስስርና ተመጋጋቢነትን ማጠናከር ላይ እንዲሁም የሀገር ውስጥ ግብአቶችን የመጠቀም ሂደትን የማስፋፋት ስራ ይሰራል፡፡ ከባድ የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ፣የኬሚካልና ፈርማሲቲካልስ እንዲሁም ከፍተኛ ቴክኖሎጂ የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች ልማትና ከሌሎች ኢንዱስትሪዎች ጋር ያላቸውን ትስስር ማረጋገጥ እን የግሉን ዘርፍ ሚና እና አጋርነት ለማሳደግ የሚያስችል አቅጣጫዎችን ይከተላል፡፡

3.አነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎችን በከፍተኛ ሁኔታ እንዲስፋፋ እና ወደ ቀጣዩ ደረጃ እንዲሸጋገሩ ለማድረግ በቂ የብድር አቅርቦት፣ ጥራት ያለው መሰረተ ልማት አቅርቦት እና በሀገሪቱ በሚገኙ በእያንዳንዱ ወረዳዎች ውስጥ ለዘርፉ ልማት የሚሆን 50 ሄክታር የመስሪያ ቦታ መሬት እንዲቀርብ እናደርጋለን፡፡ ዘርፉ ለስራ ዕድል ፈጠራ የሚያደርገውን አስተዋጽኦ እንዲያድግ በትኩረት እንሰራለን፡፡

4.የኮንስትራክሽን ዘርፍ በውጭ ግብአት ላይ ያለውን ጥገኝነት በከፍተኛ መጠን ለመቀነስ የሚያስችል የኮንስትራክሽን ግብአት አምራች ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ ይደረጋል፡፡ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ሀገራዊ አቅም በመገንባት እና የቴክኖሎጂ ሽግግር በማሳለጥ የኮንስትራክሽን ግብአቶችን የጥራት፣የወጪ እና የጊዜ ተወዳዳሪነት ቀጣይነት ባለው መንገድ በማሻሻል የሀገር በቀል ኩባንያዎች የሀገር ውስጥ ገበያ እና የክፍለ አህጉር የገበያ ድርሻ ለማሳደግ ይሰራል፡፡

5.ፓርቲያችን በማዕድን ዘርፍ የሚስተዋሉ የኢ-ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ጥያቄዎችን በመፍታት ዘርፉን በማልማት ሂደት ውስጥ የአካባቢውን ሕብረተሰብ ፍትሃዊ ተጠቃሚነት እና የአካባቢ ደህንነት ለማረጋገጥ ይሰራል፡፡

6.ማዕድንና ነዳጅ ምርት አቅራቢ ባለሀብቶች በግላቸው ወይም ከሌላ ባለሃብትና መንግስት ጋር በመንግስትና የግል አጋርነት በማስተሳሰር የምርት አቅርቦት እሴት ሰንሰለት እንዲጎለብት ይደረጋል፡፡ በአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፐራይዞች የሚመረቱ የዘርፍ ምርቶች ተገቢው እሴት ተጨምሮ ለገቢያ እንዲቀርቡ ቴክኖሎጅ የማላመድ፣የእሴት ማበልፀጊያ ማዕከላትን የማቋቋምና ሌሎች የድጋፍ ሥራዎች በስፋት እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

7.የባህላዊና አነስተኛ ማዕድናት አምራቾች እንዲደራጁ ድጋፍ በማድረግ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነታቸው እንዲያድግ እና የማዕድናት ምርትና የምርት ውጤቶች ዘመናዊ የግብይት ሥርአት እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡

8. በብዝሃ ዘርፍ እድገት በቱሪዝም ዘርፍ ያለን እምቅ አቅም ወደ ሀብትነት በመቀየር በዘርፉ የሚገኝ ኢኮኖሚዊ ተጠቃሚነት እንዲያድግ ይሰራል፡፡ በዚህም የቱሪዝም ዘርፉን የሚያነቃቁ የቱሪዝም መዳረሻዎችንና ከተሞችን የማስዋብና ለቱሪስት ቆይታ ምቹ የማድረግ፣የቱሪስት መስህቦችን የማስተዋወቅ፣የቅርስ ጥበቃ ስራችን ነባሮቹን በማጠናከር አዲሶቹን ለአለም በይበልጥ በማስተዋወቅ ሀገራችን ከአለም አስሩ የቱሪስት መዳረሻ ሀገር እንደትሆን በትኩረት ይሰራል፡፡ በዘርፉ የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብትን በመሳብ በሆቴል፣በሎጆች እና በተለያዩ የቱሪስት አገልግሎት ኢንቨስትመንቶች እንዲሳተፉ በማበረታታት የቱሪዝም መስብ ቀጠናዎችን በስብጥር ለመመስረት ይሰራል፡፡

## 2.3 አርሶ አደሩንና አርብቶ አደሩን ያማከል ጠንካራና ዘላቂ የገጠር ልማት ማረጋገጥ

1. ፓርቲያችን የአርሶ አርብቶ አደሩን ገቢን በማሳደግ በገጠር ያለን ድህነትን በመቀነስ እና ገጠሩን ለኑሮ ምቹ በማድረግ የሀገራችን ከፍተኛ ቁጥር የሚሸፍነውን አርሶና አርብቶ አደር ፍላጎቱ ተሟልቶ በተሻለ የኑሮ ደረጃ እንዲገኝ ይሰራል፡፡
2. ግብርናው ከፍተኛ ቁጥር ያለውን ሕዝብ መመገብ የሚያስችል፣ከውጭ የሚገባውን የስንዴ ምርት እና ሌሎች የግብርና ምርቶች ሙሉ በሙሉ በሀገር ውስጥ ምርት በመተካት የሚወጣውን ከፍተኛ የወጭ ምንዛሬ መቆጠብ የሚያስችል የወጭ ምንዛሬ ግኝትን የሚያሳድግ እንዲሁም የኢንዱስትሪ ግብአት አቅምን የሚጨምር እንዲሆን በትኩረት እንሰራለን፡፡

3.ግብርናን ለማዘመን የምርጥ ዘርና፣ ማዳበሪያ፣ ከጉልበት አጠቃቀም እስከ ተሻሻለ የማምረቻ መሣሪያዎች የሚዘልቅ ሜካናይዜሽን በሁሉም የግብርና ንዑስ ዘርፎች ማስፈን የሚያስችል የእርሻ መሳሪያዎች የማምረት፣የማቅረብና የማሰራጨት ቀልጣፋና ውጤታማ ሥርዓት በመዘርጋት አርሶ አደሩ ዘመናዊ የአመራረት ሂደትና ቴክኖሎጂን እንዲላመድ በማድረግ ምርታማነት እንዲጨምር ይሰራል፡፡

4. ለእንስሳት ጤናና መኖ የሚሆን አቅርቦትን በማሳደግ በእንስሳት ሃብት ልማት የአርብቶ አደሩን እና ከፊል አርብቶ አደሩን ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ ከእንስሳት ሀብት ቁጥር ይልቅ ጥራት ላይ ያተኮረ ስትራቴጂ ይከተላል፡፡

5. የአነስተኛና በየጊዜው እያነሰ የሚሄደው አማካይ የነስፍ ወከፍ የማሳና የእንስሳት እርባታ መሬት የኩታ ገጠም ውህደትን በማበረታታት የአርሶና አርብቶ አደሩን ተጠቃሚነት ለመጨመር ፓርቲያችን ይሰራል፡፡ በዚህ ረገድም በከፍተኛ ምርታማነታቸው የሚታወቁ አነስተኛ አርሶ አደሮችን የተሻለ የመሬት ይዞታ እንዲኖራቸው በማገዝ ቀስ በቀስ ወደ ኢንቨስትመንት ማሳደግ የሚያስችሉ አሰራሮችን ይተገበራል፡፡

6.የመስኖ አቅርቦት በማጎልበት የግብርናን ዘርፍ ከዝናብ ጥገኝነት ማላቀቅ የሚያስችሉ ስራዎች ይሰራሉ፡፡ ከዚህም ጋር ተያያዞ ሰፊው መስኖ እርሻዎች በግሉ ከፍለ ኢኮኖሚ ተሳትፊ እንዲለሙ በማድረግ ምርታማነት ለማሳደግ ፓርቲያችን ይሰራል፡፡

7.በገጠር ልማት ለአርሶ አደሩ የመሠረተ ልማትና ማህበራዊ ልማት ግልጋሎቶችን በማስፋት ገጠሩ ለኑሮ ምቹ እንዲሆን በማድረግና ለወጣቱ ከግብርና ውጪ የተለያዩ የስራ ዕድሎችን በመፍጠር ከገጠር ወደ ከተማ የሚድረግን ፍልሰት ጤናማ ለማድረግ የሚያስችል ስራ ይሰራል፡፡

8.በአርብቶ አደሩ አካባቢ የአርብቶ አደሩን አኗኗር ሁኔታ መሰረት ያደረገ የአርብቶ አደር አካባቢ ልማት ስራዎች ይተገብራል፡፡

9. ግብርና ፋይናንስ ኢንቨስትመንት ስርዓትን በመዘርጋት አርሶና አርብቶ አደሩ ያለበትን የፋይናንስ እጥረት በመቅረፍ ምርትና ምርታማነትን የማረጋገጥ እና የቁጠባ ባህልን የማዳበር ስራ ይሰራል፡፡

10.ፓርቲያችን የግብርና እንቅስቃሴ የተፈጥሮና ሃብት ጥበቃን የሚያጠናክር የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም ቁጥትር ክትትል ስርዓት በመዘርጋት፣ መላው ህዝብ የተፈጥሮ ልማት ጥበቃ ላይ እንዲሳተፍ የሚያበረታቱ አሰራሮችን ይቀይሳል፡፡ የተወሰኑ ይዞታዎችን ለደን ልማት የከለለ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲና መተግበሪያን ስርዓት ይዘረጋል፡፡

11.የከተማ ግብርናን በማስፋፋት ለወጣቱ የስራ ዕድል ከመፍጠር በተጨማሪ ለከተሞች በቂ እና የተመጣጠነ ምግብ በማቅረብ በከተሞች የምግብ ዋስትና ለማሳደግ በከፍተኛ ትኩረት እንሰራለን፡፡ ከዚህ አንጻር ለከተማ ግብርና የኤክስቴንሽን አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ የከተማ ግብርና የኤክስቴንሽን ስርዓት በማዘጋጀት እንዲሁም የኤክስቴንሽን ፓኬጅ በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት ስልጠና በመስጠት ግንዛቤ እንዲፈጠር እናደርጋለን፡፡

## 2.4 የአረንጓዴ አሻራ ሥራችንን በማጠናከር አረንጓዴ ኢኮኖሚ መገንባት

1. የጀመርነውን የአረንጓዴ አሻራ ሥራችንን አጠናክረን በመቀጠል ዘላቂና የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ለመገንባት ሚና እንዲጫወት እንሰራለን፡፡ በዚህም በእጅጉ እተመናመነ የመጣውን የአገራችንን የደን ሽፋን ለማሳደግ ተፈጥሮን ለመጠበቅ አረንጓዴ አሻራን የማሳደግና ተፈጥሮን ለመጠበቅ አረንጓዴ አሻራን የማሳረፍ ስራዎችን በሰፊው ይተገበራሉ፣ ከአገራችን አልፎ ቀጠናችን ከመራቆት እንዲያገግም የሚያስችሉ ንቅናቄዎች ይፈጠራሉ፡፡ በተጨማሪም ማንኛውም ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ በተፈጥሮ ዋጋ የተከፈለበት እንዳይሆን የሚያስችል የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች እና በተፈጥሮ መካከል ተስማሚነት መፍጠር የሚያስችል ስራ ይሰራል፡፡

2. የአፈር መሸርሸርን ለመቀነስና ለምነቱ እየተሸረሸረ የመጣውን መሬት እንዲያገግምና ምርታማነቱን እንዲጨምር ለማድረግ የአፈር ጥበቃና የእርከን ሥራዎች በተቀናጀና ዘላቂ በሆነ መንገድ፣ እንዲሁም አርሶ አደሩንና አርብቶ አደሩን ባሳተፈ መልኩ እንዲተገበሩ ይረዳል፡፡

3. በሃይቆቻችን፣ በወንዞቻችን እና የውሃ አካላትና ተፋሰሶቻችን ላይ የሚደርሱ ልዩ ልዩ የተፈጥሮ አደጋዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በዚህም ጤናማ የሆነ ኢኮሲስተም ለመፍጠር በጥናት ላይ የተመሰረቱ ሥራዎች በትኩረት ይሰራሉ፡፡

## 2.5 የከተማውን ህብረተሰብ መሰረታዊ የልማት ጥያቄ የሚመልስ የከተሜነት ስርዓት መገንባት

1. ከተሞች የብልጽግና ማዕከል እንዲሆኑና የከተሞች ልማት ከአዋሳኝ የገጠር አካባቢዎች ልማት ጋር ተመጋጋቢ እንዲሆኑ ይሰራል፡፡ በተጨማሪም ከተሜነትን በማሳደግ እንዲሁም ከተሞች አሳታፊ እና ዘላቂ ልማትን ባልተማከለ የከተማ አስተዳደር እንዲመሩ በማድረግ የስራ ዕድል ፈጠራ ዕድገትን እንዲያፋጥኑ ይደረጋል፡፡
2. የከተሞችን የመሬት እና የመኖሪያ ቤት አቅርቦትና አስተዳደር ስርዓት ውጤታማነት በማሻሻል ምቹ የመኖሪያ አካባቢ የመፍጠር፣ ደረጃውን የጠበቀ፣ የተቀናጀ መሰረተ-ልማትና አገልግሎት አቅርቦትን ማሻሻል፣ የከተሞች ጽዳት አገልግሎት እና የአረንጓዴ መሰረተ-ልማት ሽፋንና ተደራሽነትን በማሳደግ ከተሞች ለኑሮ ምቹ እና ተስማሚ እንዲሆኑ ለኢኮኖሚያዊ፣ ለማህበራዊና ለኢኮሎጂያዊ ተጽዕኖዎች የማይበገሩ የማድረግ ስራ ይሰራል፡፡ የከተሞችን የመሰረተ ልማት ስርጭት በተለይም የመንገድ፤ የትራንስፖርት፤ የንፁህ ውሃ እና የመብራት አቅርቦት እና ተደራሽነት ለማሳደግ መሰረታዊ ለውጥ የሚያመጡና ጥያቄዎችን ከሥራ መሰረታቸው የሚፈቱ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ ከማድረግ ባሻገር አካታች የመልሶ ልማት ስራዎች ዘላቂ የከተማ ብልጽግናን የሚረጋግጡ እንዲሆን በትኩረት ይሰራል፡፡

3.የከተሞችን ኢኮኖሚ በማሳደግ ለኢንዱስትሪ መሰረት የሚጥል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስራዎችን በማስፋፋት ስራ አጥነትን መቀነስ እንዲሁም በከተሞች የምግብ ዋስትና ስርዓትን በማስፋት ድህነትን ለመቀነስ ፓርቲያችን አበክሮ ይሰራል፡፡

4.ፓርቲያችን በከተሞች የመኖሪያ ቤት ችግሮችን ለመቅረፍ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ያካተተ የመንግስትና የግል አጋርነትን በመከተልና በተቀናጀ ቤቶች ልማት መኖሪያ ቤቶች እንዲሰሩ የሚያደርግ ሲሆን በገጠር ማዕከል ከተሞች በተለይም የኢንዱስትሪ ፓርኮች ያሉባቸው እና የነዋሪዎች ቁጥር መጨመር የሚታይባቸው የገጠር ማዕከል ከተሞች ላይ ቤቶች እንዲገነቡ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም በከተሞች የሚታየውን የቤት ሽያጭ እና ኪራይ ከገበያ መርሃ ውጪ በከፍተኛ ሁኔታ የዋጋ መናር የሚታይባቸውና የነዋሪዎችን አቅም የሚፈታተንበት ደረጃ የደረሰ በመሆኑ የቤት ግዢ እና ሽያጭ የተረጋጋ እንዲሆን አሰራር እና መመሪያ በማዘጋጀት ነዋሪዎች ተመጣጣኝ የቤት ኪራይ እንዲያወጡ ለማድረግ ፓርቲያችን በቁርጠኝነት የሚሰራ ይሆናል፡፡

5.አዳዲስ የኢኮኖሚ ኮሪደር ሊሆን የሚችሉ ከተሞችን በማሳደግ በውስን ከተሞች ላይ ያለውን የነዋሪዎች ብዛት መቀነስ የሚያስችል ስራዎች በትኩረት የሚሰራባቸው ይሆናሉ፡፡ በዚህም መሰረት ልማት አቅርቦት ከእድገት ማዕከሎች ጋር በማቆራኘት እንዲያድግ ይደረጋል፡፡

6.የከተሞች የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ተገልጋዮችን የሚያረካ ቀልጣፋና ተደራሽ አስራርን ለመፍጠር የሚያስችል ያልተማከለ የከተሞች አስተዳደርን የማስፋት አሰራርን በቴክኖሎጂ የማዳበር እና የመረጃ ልውውጥን ወደ ዲጂታል ማሳደግ ሂደትን የተከተለ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

## 2.6 የድህውን የኑሮ ሁኔታና ደረጃ ያገናዘበ የዋጋ መረጋጋት ማስፈን

1. ፓርቲያችን በቋሚ ገቢ የሚተዳደረው እና ዝቅተኛ ገቢ ህዝብ በዋጋ ግሽበት እንዳይጎዳ ዋጋን የማረጋጋት ዘላቂ ስራ ይሰራል፡፡ ለዋጋ ንረት መባባስ ዋነኛው መንስኤ የሆነውን የምርታማነት ችግር በመቅረፍ የፍጆታ ሸቀጦች ምርትና አቅርቦት በሃገር ውስጥ ከፍ ለማድረግ የሚያስችል የመንግስትና የግል ዘርፍ ጥምረት ለማምጣት በልዩ ትኩረት ይንቀሳቀሳል፡፡
2. በገበያው ላይ እጥረት የሚታይባቸውን ሸቀጦች መንግስት በራሱ ሸቀጦችን ለህዝብ የማቅረብ እርምጃ በመውሰድ ገበያን ለማረጋጋት ከሚደረገው ጥረት ባሻገር የአቅርቦት እጥረት ያለባቸው ሸቀጦች ላይ ለሚሰማሩ አምራቾች ልዩ ማበረታቻ በመስጠት እጥረት ያለባቸው ምርቶች ከፍ ባለ መጠን እንዲመረቱ በማድረግ ህብረተሰቡ በአነስተኛ ዋጋ የተለያዩ ሸቀጦችን እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡
3. ፓርቲያችን አርቴፊሻል የዋጋ ንረትን እና የገበያው ሰንሰለት በመርዘሙ ምክንያት የሚፈጠሩ የዋጋ ግሽበትን ለመከላከል ገበያው በህግ እንዲገዛ የሚያደርግ ቁጥጥር ላይ በአጽኖት ይሰራል፡፡
4. ከአምራች ወይም ከአቅራቢ እስከ ተጠቃሚ ድረስ ያለውን የገበያውን ሰንሰለት ተሳታፊዎች ቁጥር እንዲቀንስ በማድረግ ምርቶች ከአምራች ወይም ከአቅራቢ በቀጥታ ወደ ተጠቃሚ እንዲደርስ የሚያደርግ የአሰራር ስርዓት ያበጃል፡፡ አላስፈላጊ የግብይት ሰንሰለቶችን በማስወገድ የሀገር ውስጥ የምርት ግብይት ስርዓትን ቀልጣፋና ተወዳዳሪ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

## 2.7 ጥራቱን የጠበቀ ፍትሃዊ የመሰረተ ልማት ስርጭት ማረጋገጥ

1. የመሰረተ ልማት ስርጭት ለኢንደስትሪው መስፋፋትና እሱን ተከትሎ የሚመጣው ከተሜነት የሚፈልገውን ከፍተኛ የመሰረተ ልማት ሊያሟላ የሚችል እንዲሁም ገጠርን ምቹ መኖሪያ የማድረግ ሂደታችንን የሚያግዝ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ የመሠረት ልማት ዝርጋታዎች ጥራትና ቅልጥፍናን የተላበሱ ሆነው ፍትሃዊ ተደራሽነትንና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታን የሚያረጋግጡ እንዲሆኑ ይደርጋል፡፡
2. የመሰረተ ልማት ስርጭትን በማስፋፋት በሀገራችን የመንገድ፣ የኤሌትሪክና የቴሌኮም መሰረተ-ልማቶችን ሽፋን ለማሳደግ ፓርቲያችን በትኩረት ይሰራል፡፡ በዚህ ሂደት በየክልሎች የሚታየውን ያልተመጣጠነ የመሰረተ ልማት ስርጭት የሚያርም የተመጣጠነ የመሰረተ ልማት ስርጭት እንዲኖር ያደርጋል፡፡ በክልሎች ውስጥ ከማዕከል ርቀው በሚገኙ እንደ አርብቶ አደር አካባቢዎች የመንገድ፣ የመብራት እና ሌሎች የመሠረተ ልማቶች ፍትሃዊ ስርጭት ክፍተትን የሚያርም አሰራር በመተግበር በሁሉም አካባቢ የመሰረተ ልማት ተደራሽነት እንዲያረጋግጥ ይደረጋል፡፡
3. ፓርቲያችን የመሰረት ልማት የጥራት ክፍተቶችንም ለማረምና አዳዲስ የሚሰሩ መሰረተ ልማቶች ጥራታቸውን የጠበቁ እንዲሆን ለማድረግ በልዩ ትኩረት ይሰራል፡፡ የመሰረተ ልማት ልማት መስፋፋት ከጥራት ጋር እንዲሆን ለማድረግ በልዩ ትኩረት የፕሮጀክት አፈፀፀም ችግሮች የሆኑ ብልሹ አሰራሮችና ሌብነት በማሰወገድ ፕሮጀክቶች በተባለበት ጊዜ እና በተመደበላቸው ገንዘብ እንዲፈጸሙ ይሰራል፡፡

4. የትራንስፖርት መሰረተ ልማት የተቀናጀ፣ፍትሃዊና ተደራሽ ከማድረግ ባሻገር ደህንነቱ የተጠበቀ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት የሚያስችል እንዲሁም ምርታማነትን የሚያሳልጥ ቀልጣፋና አስተማማኝ የሎጂስቲክስ አገልግሎት አሰራር ሥርዓት የሚዘረጋ ይሆናል፡፡

5.ፓርቲያችን የሀገራችን ኢኮኖሚ ፈጣን እድገት እንዲሁም እየጨመረ የሚመጣውን የኤሌትሪክ ሃይል አቅረቦት ፍላጎት በወቁቱና በአስተማማኝ ለማቅረብ የሚያስችል የኃይል መሠረተ ልማት ይገነባል፡፡ በኢነርጂ መስክ በፍላጎትና አቅርቦት መካከል ያለውን ክፍተት በማጣጣም አቅምን ያገናዘብ ፍትሃዊ የኢነርጂ ተደራሽነትን ከማረጋገጥ ባሻገር አሁን ያለውን ዝቅተኛ የነፍስ ወከፍ ዓመታዊ ፍጆታ በማሳደግ ለወጪ ንግድ በሚበቃ ሁኔታ አቅርቦቱን በማሳደግ እና በመላ ሀገሪቱ በማስፋፋት ለሁሉም አካባቢዎች እንዲዳረስ ለማድረግ ሀገር አቀፍ የኤሌትሪክ ኃይል ማመንጨትን በሶስት እጥፍ ለማሳደግ ይሰራል፡፡ በተጨማሪም ኦፍጊሪድና ጊሪድ አማራጮችን በመጠቀም በአምስት አመቱ መቶ በመቶ የመብራት አቅርቦት ለማድረስ ይሰራል፡፡

ይህም እንዲሆን አስተማማኝ የኤሌትሪክ ኃይል መሰረተ ልማት መገንባት፣ በቂ ኢንቨስትመንት ማከናወን እና ጤናማ ተቋማዊ የፋይናንስ አቅም እንዲኖር ለማድረግ በትኩረት ይሰራል፡፡ ባለሀብቶች በዘርፉ ኢንቨስት እንዲያደርጉ የማበረታታት ስራ በሰፊው ይሰራል፡፡

6. ፓርቲያችን የመጠጥ ውሃ፣ ሳኒቴሽንና ኃይጂን አቅርቦቱን በማስፋፋትና በአገልግሎቱ ተደራሽ ያልሆነውን ህዝብ ተጠቃሚ በማድረግ፣ ንፁህ፣ አስተማማኝና በቂ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ለሁሉም ዜጎች እንዲዳረስ ያደርጋል፡፡

7. የመካከለኛና ሰፋፊ የመስኖ ልማት መስፋፋት ስትራቴጂን በማጠናከር እና የበጀት ድርሻውን ከፍ በማድረግ ለመካከለኛና እና ሰፋፊ የመስኖ አውታሮች ግንባታ ልዩ ትኩረት ይሰጣል፡፡የመካከለኛና ሰፋፊ የመስኖ አውታሮችን በማስፋፋት እና የተሻሻሉ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የገበሬውን ምርታማነት ከመጨመር በተጨማሪ የግብርና የስራ እድል ፈጠራን ለተማሩና መለስተኛ ሙያ ላላቸው ወጣቶች እንዲዳረስ ያደርጋል፡፡

## 2.8 ለቀጣዩ ትውልድ ዕዳን የማያወርስ ዘላቂ የልማት ፋይናንስ ማረጋገጥ

1. የድህነት አዙሪትን በመስበር ወደሌላ የፍላጎት ደረጃ የሚያሻግር የብልፅግና ጉዞ ለዘላቂ የልማት ፋይናንስ ትኩረት መስጠት እንደሚያስፈልግ ፓርቲያችን ያምናል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የመንግስት የልማት ወጪ አሸፋፈን ሀላፊነት የተሞላበት የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ የሚፈልግ፣የወደፊት የብድር ጫና የሚያስፈራው ስለመጪው ትውልድ አሻግሮ የሚያይ እና በእውቀት የሚመራ መሆን አለበት ብሎ በጥብቅ ያምናል፡፡ በመሆኑም ፓርቲያችን ለዚህ ግብ መሳካት በልዩ ትኩረት የሚሰራ ይሆናል፡፡ ፓርቲያችን ለመጪው ትውልድ ወረትን እንጂ ውዝፍ እዳን አያወርስም፡፡ ስለዚህም ዘላቂ የሆነ የልማት ወጪ አሸፋፈን ስልትን ይተገብራል፡፡
2. ዘመናዊ አስራርና ተወዳዳሪ የሰፋነበት መሠረትዊ አቅጣጫዎች ላይ ያተኮረ የፋይናንስ ዘርፍ ሪፎርም ያደርጋል፡፡ ይህም ሲሆን በሁሉም የስራ መስክና የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ ያሉ የሕብረተስብ ክፍሎችን አካታች የሆነ የፋይናንስ አገልግሎትን በማስፋፋትና እና ተደራሽ እንዲሆን በማድረግ የዜጎችን የኢኮኖሚ አቅም ማጎልበት ላይ ልዩ ትኩረት በማድረግ ይሰራል፡፡ በዚህም የሀገር ውስጥ ቁጠባን በማሳደግ ዘላቂ የሆነ የልማት ፋይናንስ እንዲያጎለብቱ ይሰራል፡፡
3. የሀገር ውስጥ ገቢን ለማሳደግ ታክስ በፍቃደኝነት የመክፈል ባህልን የማዳበር፣ዲጂታል የገቢ አስተዳደር ሥርዓትን መገንባት፣ኮትሮባንድ፣ታክስ ማጭበርበር እና ህቡዕ ኢኮኖሚን ወደ ታክስ ሥርዓት ማምጣት፣ምቹ የስራ ከባቢ፣ብቁ፣ተነሳሽነት ያለው እና ታማኝ የሆነ አመራር እና ስራተኛ እንዲፈጠር ፓርቲያችን በትጋት አበክሮ ይሰራል፡፡

## 2.9 ዲጅታል ኢኮኖሚ ማስለጥ የሚያስችል የቴክኖሎጂ አቅም መገንባት

1. ጉልበትን መሠረት ካደረገ የአመራረት ዘዴ በሂደት የቴክኖሎጂን ፈጣን ተለዋዋጭነት ታሳቢ ያደረገ የግብርናና የማኑፋክቸሪነግ ኢንዱስትሪ መሰረትን የመጣል፣ቴክኖሎጂና ዕውቀትን በማጣመር የአገልግሎት ዘርፍ ኢኮኖሚ የመገንባት፣ የቴክኖሎጂና የኢኖቤሽን ተወዳዳሪነትን የማሳደግ ስራዎች ፓርቲያችን በትኩረት የሚሰራባቸው መስኮች ናቸው፡፡ ዘመናዊና አለምቀፍዊ የዲጅታል ኢኮኖሚን ለመገንባት የሚያስችል የኢኖቤሽንና ቴክኖሎጂ መሠረት ልማቶችንና መረጃዎችን እንዲለሙና ተደራሽነታቸውን እንዲሰፋ እንዲሁም የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎቶችን በፍጥነት እንዲያድጉ ይደረጋል፡፡
2. ፓርቲያችን ለምርምርና ቴክኖሎጂ ልማት አገልግሎት የሚውሉ መሰረተ ልማቶችን የመገንባት እና የማደራጀት፣አላስፈላጊውን የሰው ሀብት አቅምን የማሳደግ ስራን ፓርቲያችን ይሰራል፡፡ የሀገር በቀል ዕውቀቶች በቴክኖሎጂ እንዲለሙና ለሀገራዊ የኢኖቬሽን ልማት አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ የሚያደርግ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡
3. ምርትን እና ምርታማነትን የሚያሻሽሉ ምርምሮች የማካሄድ፣ቴክኖሎጂዎችን የማልማት፣ችግር ፈቺ ቴክኖሎጂዎችን የማላመድ፤የለሙ ቴክኖለጂዎችን የማስፋፋት እና በኢኮኖሚ ውስጥ ጉልህ ሚና የሚኖራቸውን የምርምር ቴክኖሎጂና የኢኖቬሽን ውጤቶችን የማበረታታት ስትራቴጂዎች ይተገበራሉ፡፡
4. ፓርቲያችን የቴክኖሎጂ መሰረት ልማት በማሳደግ የስራ ዕድል የመፍጠር እና የቴክኖሎጂ ኢንተርፕራይዞችን በማበረታታት ሀብት የማፍራት አቅጣጫዎች በመከተል ቴክኖሎጂ እንዲስፋ በዘርፉም የስራ ዕድል እንዲፈጠር ይሰራል፡፡

## ምዕራፍ ሶስት
## የህዝባችንን ፍላጎት የሚያሟላ ፍትሐዊ ማህበራዊ አገልግሎት ሥርዓት መዘርጋት

**የአምስት ዓመት የፓርቲያችን የማህበራዊ ብልፅግና የማረጋገጥ ግቦች፣**

- ጥራትና ፍትሐዊ ተደራሽነትን ያማከለ የትምህርት ሥርዓት መዘርጋት
- መከላከልንና አክሞ ማዳንን መሰረት ያደረገ የማይበገር የጤና ሥርዓት መዘርጋት
- የሴቶች፣ ህፃናት እና ወጣቶች መብት፣ ውክልና እና የልማት ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ
- የማህበራዊ ደህንነትና ዋስትና ስርዓታችንን ማጠናከር
- የባህል፣ ቱሪዝምና ስፖርት ልማትን ማረጋገጥ

ሀገራችን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እድገት መነሻዋ ዝቅተኛ ደረጃ በመሆኑ ሁለንተናዊ ማኅበራዊ ብልፅግና የማረጋገጥ ጉዳይ የኢኮኖሚያችን ማጠንጠኛ እምብርት ይሆናል፡፡ በመሆኑም የማኅበራዊ ልማት ስራዎችን የእድገትና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት መንትያ ግቦችን የማሳካት ጉዳይ ይሆናል፡፡ የማኅበራዊ ልማት ስራዎቻችን ከችሮታና ከነባሩ የማኅበራዊ ደህንነት ትኩረት ወጥቶ ችግሩን ከመብት አንፃር የሚመለከተው ይሆናል፡፡ ምንም እንኳን ማኅበራዊ ልማት በሀገራችን ኢኮኖሚያዊ አቅም የሚወሰን ቢሆንም እንደአካሄድ ግን በግርድፉ ጉዳዩን ከችሮታ ጋር ከማስተሳሰር ጉዳዩን በመብት መነጽር እየተመለከትን ከአገሪቱ ኢኮኖሚ አንጻር በትኩረት መልስ የምንሰጠው ይሆናል፡፡

ፓርቲያችን የሀገራችን ህዝቦች ሁለንተናዊ ማህበራዊ ብልፅግና ለማረጋገጥ እና በመጪዎቹ ዓመታት ኢትዮጵያ ሀገራችንን በሁሉም መስክ አፍሪካዊ የብልፅግና ተምሳሌት ለማድረግ የሚሰራ ሲሆን ማኅበራዊ አገልግሎቶችን በጥራት ተደራሽ በማድረግ፣ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን መብት በማስከበርና ተሳትፏቸውን በማሳደግ እንዲሁም ለችግር ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችን ከአስከፊ ኑሮ የሚጠብቅ የማኅበራዊ ጥበቃ ስርዓት በመተግበር ማኅበራዊ ብልፅግናና ለማረጋገጥ የሚሰራ ይሆናል፡፡

## 3.1 ጥራትና ፍትሐዊ ተደራሽነትን ያማከሉ የትምህርት ስርዓት መዘርጋት

1. የትምህርት ጥራትን እና ተገቢነትን በሁሉም ደረጃ በማሻሻል ሁሉም ህፃናትና ወጣቶች ሙሉ አቅማቸውን እንዲጠቀሙ የሚያስችል የትምህርት ስርዓት እንዲኖር እንሰራለን፡፡ የሀገራችን ሥርዓተ-ትምህርት፣ የማስተማር ስነ-ዘዴው፣ የማስተማሪያ እና የመማሪያ ቁሳቁሶች እና ግምገማ ስርዓቶቹ እንዲያሻሽሉና ከገበያው ፍላጎት ጋር የተጣጣሙ እንዲሆኑ በማድረግ ሁሉም የሀገራችን ተማሪዎች ከፍተኛ አፈፃፀም ካላቸው ዓለም አቀፍ ሥርዓቶች ጋር የሚነፃፀሩ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ውጤቶችን ማስመዝገብ የሚችሉበት የትምህርት ሥርዓት እንዲኖር ይደረጋል፡፡
2. በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች በገጠር፣ በከተማ፣ በፆታ፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዳራ፣ በአካል ጉዳተኝነት፣ በስጦታ እና ተሰጥኦ ምንም ይሁን ምን ልዩነት ሳይፈጠር ሁሉም ዜጎች ትምህርት እንዲያገኙ የትምህርት ፍትሀዊ ተደራሽነት ላይ በትኩረት የምንሰራ ይሆናል፡፡
3. በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ ቅልጥፍናን እና ውጤታማነትን ለማሻሻል የተጠያቂነትን፣ የግልጽነኝነት እና የባለቤትነት ስሜትን የሚፈጥር ሥርዓት ለመገንባት ይሰራል፡፡ በዚህም የትምህርት አመራሩንና አስተዳደሩን በሚጠናከርና አቅሙን በማጎልበት ብቃትና ውጤታማነት እንዲሻሻልና ተጠያቂነት፣ ግልፀኝነትንና ባለቤትነትን የሚያረጋግጥ አሰራር በመዘርጋት በትምህርት ሥርዓቱ መልካም አስተዳደር እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡
4. ብሔራዊ አንድነትን የሚያጠናክር የግብረ ገብ ትምህርት በአንደኛ ደረጃ ስርዓተ ትምህርት ውስጥ እንዲካተት በማድረግ እንዲሁም ተማሪዎች ለማህበረሰቡ የሚሰጡትን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እንዲጎለብት በማድረግ በትምህርት ተቋማት እና በማህበረሰቡ መካከል ያለውን ግንኙነት እንዲጠናከር፣ በመልካም እሴቶቸች የታነጹ በሁለንተናዊ ስብዕናቸው ብቁ የሆኑ ዜጎችን ማፍራት የሚችል የትምህርት ሥርዓት እንዲኖር ይደረጋል፡፡
5. የግል ዘርፉ የትምህርት ግብዓቶችን ማምረት እንዲሁም በትምህርትና ስልጠናው ዘርፍ ላይ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርግ በማበረታታት እና የትምህርትና ስልጠና ስርዓቱን በሃብት ለመደገፍ የሚያስችል የትምህርት ልማት ባንክ እንዲቋቋም በማድረግ፣ በትምህርት ዘርፍ የመንግስት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ እና የግል ባለድርሻዎች አጋርነት እንዲጠናከር እንሰራለን፡፡
6. ለትምህርት ጥራት መሻሻል በሁሉም ደረጃ ላይ የሚመደቡ መምህራን ሚና ወሳኝ በመሆኑ መምህራን የተሻለ ችሎታና ስነ ምግባር እንዲኖራቸው ልዩ ትኩረት እንሰጣለን፡፡ የመምህርነት ሙያ የሚገባውን የትውልድ ቀራጭነት ክብር እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡ በየደረጃው ያሉ መምህራን የሚያገኙት የሙያ ክፍያ እና ጥቅማጥቅም እንዲሻሻል በልዩ ሁኔታ ይሰራል፡፡
7. የከፍተኛ ትምህርት ተደራሽነትን በማስፋት እና ፍትሀዊነቱን በማረጋገጥ ተማሪዎችና ሰልጣኞች ልዩነት ሳይደረግባቸው በሚመርጧቸው የትምህርት መስኮች ሊገቡ በሚችሉበትን እድል ለማስፋት እንሰራለን፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና በቴክኖሎጂ የታገዘ የትምህርት አቀራረብ አማራጮች እንዲስፋፋ በማድረግ በፍላጎትና በችሎታ ላይ የተመሰረተ የትምህርት ተደራሽነትን እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡
8. ኢንዱትሪና ሴክተር መስሪያ ቤቶች ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር የሚኖራቸው ትስስር እንዲጠናከር የሚያደርግ ሥርዓት በመዘርጋት ተማሪዎች በተግባር የተደገፈ ትምህርት እንዲወስዱና ያላቸውን የሙያ እድገት ከኢንዱስትሪዎች ፍላጎት ጋር የተጣጣመ በማድረግ፣ የከፍተኛ ትምህርት ተመራቂዎች የመቀጠር ምጣኔ እንዲያድግ እንሰራለን፡፡
9. የሳይንስ ባህል ለመገንባት የሚያስችሉ የቴክኖሎጂ እድገትና ሽግግር፣ የማህበረሰብ አገልግሎት ለማዳበርም የሚያስችሉ ችግር ፈቺ የሆኑ የሀገር በቀል እውቀቶች፣ የሳይንስ እውቀት ፈጠራ፣ ሽግግርና ማስፋፋት የሚያስችሉ ስርዓቶችን ይዘረጋሉ፡፡ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነትን ለማጎልበት የተጠናከረ የአይሲቲ መሰረተ ልማት ዝርጋታ፣ የቴክኖሎጂ ፈጠራና ሽግግር ማካሄድ፣ ቴክኖሎጂን ማዳበርና ማበልፀግ እንዲሁም የሰው ሰራሽ ብልሀት (Artificial Intelligence) ማሳደግ በትኩረት የምንሰራባቸው ጉዳዮች ይሆናሉ፡፡
10. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የመካከለኛ ባለሙያዎች መፍለቂያና በተግባራዊ ስልጠና ብቁ ባለሙያዎች በሚፈጥሩባቸው እንዲሆኑ ከተደራሽነት በላይ ጥራት ላይ በትኩረት እንዲሰሩ እና በቴክኖሎጂ እና በችግር ፈቺ ፈጠራዎች ላይ የሚሰማሩ ወጣቶች ማፍለቂያ ተቋማት እዲሆኑ ይሰራል፡፡

## 3.2 መከላከልንና አክሞ ማዳንን መሰረት ያደረገ የማይበገር የጤና ሥርዓት መዘርጋት

1. ሁሉን አቀፍ የጤና አገልግሎት ሽፋን ትግበራን በማፋጠን የጤና ተቋማት ተደራሽነት እንዲያድግ ፓርቲያችን ይሰራል፡፡ በተለይም የተደራሽነት ችግር ያለባቸው የአርብቶ አደር አካባቢዎች ላይ ልዩ ትኩረት በመስጠት የምንሰራ ይሆናል፡፡
2. የጤና ፋይናንስ ሥርዓትን በማጠናከር በማህበረሰብ ጤና መድህን ሥርዓት የታቀፈ ቤተሰቦችን እና በማህበራዊ የጤና መድህን የታቀፉ ሰራተኞችን በከፍተኛ ሁኔታ ለማሳደግ በትኩረት እንሰራለን፡፡
3. ወረርሽኞችን በዘላቂ ሁኔታ ለመከላከል የሚያስችል ልዩ የወረርሽኝ መከላከል ሥርዓት በመዘርጋት የማህበረሰብ ጤና ድንገተኛ አደጋዎች እና ወረርሽኝ የመቋቋም አቅም ያለው የጤና ሥርዓትና የአደጋ ስጋት አስተዳደር ለመገንባት በትኩረት ይሰራል፡፡
4. ለእናቶች የሚሰጠውን የጤና አገልግሎት ጥራትና ተደራሽነትን በማሻሻልና የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ምጣኔ በማሳደግ የእናቶችና ህፃናት ሞትን በከፍተኛ ሁኔታ ለመቀነስ በልዩ ትኩረት ይሰራል፡፡ ከአምስት አመት በታች ያሉ ህፃናት የመቀንጨር እና በመውለድ እድሜ ክልል ውስጥ በሚገኙ ሴቶች የሚከሰት የደም ማነስ በሽታ እንዲቀነስ ይደረጋል፡፡ የዜጎች አማካይ በሕይወት የመኖር እድሜን ለማሳደግ ይሰራል፡፡
5. የግል እና አካባቢን ንጽህና አጠባበቅ ለማሳደግ በከተማም ይሁን በገጠር መሰረታዊ የመፀዳጃ ቤት አጠቃቀም ለማሻሻል ልዩ ትኩረት ይሰጠዋል፡፡ በዚህም መሰረታዊ የመፀዳጃ አገልግሎት ያላቸው ቤተሰቦች ሽፋን ለማሳደግ ፓርቲያችን ይሰራል፡፡
6. ተላላፊ በሆኑ በሽታዎች ምክንያት የሚደርሰውን ሞት ለመከላከልና ለመቀነስ የኤች አይ ቪ ምርመራ ለማሳደግ፣ አዲስ በኤች አይ ቪ ኤድስ ቫይረስ የሚያዙ ሰዎችን መጠን ለመቀነስ እና የኤች አይ ቪ ቫይረስ ከእናት ወደ ልጅ የመተላለፍ ስርጭትና ሞት ምጣኔ ለመቀነስ እንዲሁም የፀረ-ኤች-አይ.ቪ/ኤ.ድ.ስ ህክምና አገልግሎት ያገኙ ሰዎች ሽፋን ለማሳደግ እንሰራለን፡፡ በተጨማሪም ቲቪ፣ የሥጋ ደዌና ወባ በሽታዎች ስርጭትን ለመቀነስ ይሰራል፡፡ በወባ በሽታ ሳቢያ የሚደርሰውን የሞት መጠን በቀጣይ አምስት ዓመተ ሙሉ በሙሉ ለማስወገድ በልዩ ትኩረት እንሰራለን፡፡
7. ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ምክንያት የሚከሰት ህመምን እና ሞትን ለመከላከል በቂ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ እንዲስፋፋና ባህል እዲሆን ለማድረግ፣ የአደንዛዥ ዕፅ ተጠቃሚ የሆኑ ሰዎችን እንዲቀንስ ለመቀነስ፣ ከ15 ዓመት በላይ በሆናቸው ሰዎች የሚከሰት የደም ግፊት በሽታን ለመቀነስ፣ የማህጸን በር ጫፍ ካንሰር ልየታ አገልግሎት ተደራሽነትን ለማሳደግ እንዲሁም ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ምክንያት የሚከሰት ከእድሜ ቀድሞ የሞት መጠን ለመቀነስ ፓርቲያችን በትኩረት ይሰራል፡፡
8. የጤናው ዘርፍ ስኬታማ ለማድረግ የሠው ኃይል ልማትና አስተዳደር በማሻሻል ጥራትን ማዕከል ያደረገ የጤና ባለሙያ እና ሐኪም ተደራሽነትን እንዲጨምር ይደረጋል፡፡
9. የግሉ ዘርፍ በህክምና ላይ በተለይም በህክምና ቱሪዝም ስፔሻሊቲ ላይ እንዲሰሩ በልዩ ትኩረት ድጋፍ የሚደረግለት ሲሆን ትውልደ ኢትዮጵያዊ ባለሙያዎች ሀገራችን በህክምና ቱሪዝም ውጤታማ እንድትሆን በዘርፉ እዲሳተፉ ማበረታቻ ይደረግላቸዋል፡፡

## 3.3 የሴቶች፣ ህፃናት እና ወጣቶች መብት፣ ውክልና እና የልማት ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ

1. ሴቶችን ማብቃትና በስርዓተ ፆታ እኩልነት ሴቶች እኩል ዕድል የማግኘት መብታቸውና ከማናቸውም ከማንኛውም ጥቃትና መድሎ የተጠበቁና በሁሉም መስክ ተሳትፎና ተጠቃሚነታቸው ለማረጋገጥን አልመን እንሰራለን፡፡
2. የሴቶችን እና ህፃናትን ጥበቃ ሥርዓት በማጠናከር ሁለንተናዊ ደህንነታቸውን ማስጠበቅ እና መብታቸውን ማስከበር በሙሉ ትኩረት የሚሰራ ይሆናል፡፡ በሴቶችና ህፃናት ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲወገዱና እንዲቀንሱ ለማድረግ ብሔራዊ የጥቃት አድራሾች መረጃ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ ስርዓተ-ፆታ ላይ መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን ለመከላከል የመንግስት ዜሮ የመታገስ አቋም ተግባራዊ ለማድረግ ጥቃት የተፈፀመባቸው ሴቶችና ህፃናት በልዩ ሁኔታ የሚመረምሩ እና ጥቃትን ለመከላከል የሰለጠኑ የፖሊስ አባላት ያሉት ግብረ-ሀይል ይቋቋማል፡፡ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙ ህፃናት የተጠናከረ ድጋፍ ለማድረግ የህፃናት ማህበራዊ አገልግሎት ኤጀንሲ ተቋቁሞ የኬዝ ማኔጅመንት ሥርዓት ይተገበራል፡፡
3. **የሴቶች ልጅ ግርዛትና የህፃናት ጋብቻን ለማስቀረት ሁሉንም ያሳተፈ ንቅናቄ በየደረጃው በማካሄድ ቋሚ የሆኑ ትምህርታዊ ፕሮግራሞች በሚድያ ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆን በማድረግ የሴት ልጅ ግርዛትና የህፃናት ጋብቻ በከፍተኛ ሁኔታ እንዲቀንስ እናደርጋለን፡፡**

4. በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ህፃናት በሀገር ውስጥ ያለውን አማራጭ በመለየትና በማስፋፋት ለመደገፍ የሚያስችል የህፃናት ማህበራዊ አገልግሎት ሥርዓት በመዘርጋት በአማራጭ ፕሮግራሞች ድጋፍ የሚደረግላቸው ህፃናት እንዲያድግ ይደረጋል፡፡ ጥቃት ለሚደርስባቸው ሴቶችና ህፃናት አገልግሎት የሚሰጡ የአንድ መስኮትና የተሃድሶ መስጫ ማዕከላትን በማቋቋም፣ በማስፋትና በማጠናከር የህግ፣ ማህበራዊ፣ ስነ-ልቦናዊ ኢኮኖሚያዊ የድጋፍ አገልግሎቶች ተጠቃሚ የሚሆኑ ሴቶችና የህፃናት ምጣኔ እንዲያድግ የሚደረግ ሲሆን ከቤተሰብና ማህበረሰብ በተለያየ ምክንያት የተለዩ ህፃናት የማዋሀድና የማቀላቀል ተግባራት በትኩረት እንሰራለን፡፡ የህፃናት ማቆያዎች በሁሉም የመንግስት ተቋማት፣ በግሉ ዘርፍና በማህበረሰብ ደረጃ እንዲስፋፋና እንዲጠናከሩ ለማድረግ ይሰራል፡፡
5. በወጣቶች ማብቃትና ተሳትፎ ዙሪያ ወጣቶችን ያማከለ የአቅም ግንባታ ስራዎችን በማከናወን ወጣቶች እምቅ አቅምና ችሎታቸውን አውጥተው በመጠቀም በሁሉም መስኮች ተሳታፊ፣ ተወዳዳሪና ተጠቃሚ እንዲሆ ማድረግ ላይ በትኩረት ይሰራል፡፡ ሴቶችንና ወጣቶችን በአመራርና በውሳኔ ሰጪነት ሚና በህግ አውጪና በህግ ተርጓሚ የሚኖራቸው ስፍራ ለማሳደግ በትኩረት ይሰራል፡፡

   አገር አቀፍ የወጣቶች ካውንስል የሚቋቋምበትን ሁኔታ በማመቻቸት ወጣቶች ውክልና እንዲኖራቸው ብልፅግና ፓርቲ ይሰራል፡፡ የወጣቶች የግንኙነትና የመረጃ ማዕከል ዩዝ ኮኔክት ፕሮግራም በመተግበር ወጣቶች ከአፍሪካና አለምዓቀፍ አቻዎቻቸው ጋር ትስስር የሚፈጥሩበት እድል ይመቻቻል፡፡ ወጣቶች ከሱስ የሚያገግሙበት የወጣቶች የሱስ ማገገሚያ ማዕከላትን እንዲስፋፉ ይደረጋል፡፡
6. የልማት ፈንድ በማቋቋም ስራ ፈጣሪ ሴቶች በተለያዩ ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ፈንዶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ ፍትሃዊ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነታቸውን የማረጋገጥና የማስተሳሰር ስራ የሚከናወን ሲሆን ሴቶች በብድር፣ በህብረት ስራ ማህበራት፣ በገጠር መሬት ባለቤትነት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በልዩ ትኩረት ብልፅግና ይሰራል፡፡ ለሴቶች ተስማሚ የሆኑ ጊዜና ጉልበት ቆጣቢ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን ከአፍላቂ ተቋማት ጋር በመተባብርና በመቀናጀት የመለየትና ሴቶች በቴክኖሎጂዎቹ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ እንሰራለን፡፡

## 3.4 ማህበራዊ ደህንነትና ዋስትና ሥርዓታችንን ማጠናከር

1. ሠላማዊ የኢንዱስትሪ ግንኙነትን ለመፍጠርና በዘላቂነት ለማሻሻል የአሰሪዎችና የሰራተኞች በማህበር መደራጀትን ለማሳደግ ይሰራል፡፡ በድርጅት ደረጃ የሁለትዮሽ የሥራ ቦታ ትብብርና ማህበራዊ ምክክር ሥርዓቶችን እንዲያድግ እና የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አማካሪ ቦርድ በሁሉም ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች እንዲቋቋም በማድረግ ለአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የሚቀርቡ የሥራ ክርክሮች በስምምነት እንዲፈቱ ለማድረግ እንሰራለን፡፡ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ለመከላከል ብሔራዊ ፕሮግራሞች በመዘርጋት እና በሥራ ቦታ ቁጥጥር በማድረግ አስከፊ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛን ለማስወገድ እንሰራለን፡፡ የሙያ ደህንነትና ጤንነት አገልግሎት ለማጠናከርና ለማስፋፋት የሙያ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ኤክስቴንሽን አገልግሎትና ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ተደራሽ ማድረግ፣ በሥራ ላይ ሊደርሱ የሚችሉ የሥራ ላይ አደጋዎችና የሙያ በሽታዎችን በዘላቂነት ለመከላከል እና ሰብአዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስን ለመቀነስ እንሰራለን፡፡
2. ቀልጣፋ፣ ፍትሃዊና ተደራሽ የሥራ ስምሪት አገልግሎቶችን በከፍተኛ ደረጃ እንዲስፋፋ ይደረጋል፡፡ የሥራ ስምሪት ድጋፍ አግኝተው በሥራ ላይ የሚሰማሩ ዜጎች ቁጥር እንዲያድግ በማድረግ ሥራ አጥነትን ለመቀነስ እንሰራለን፡፡ የማህበራዊ ዋስትና ሽፋንና የጡረታ ፈንድን ለማሳደግ የግል ድርጅት ሠራተኞችን ምዝገባ እንዲያድግ ይደረጋል፡፡ የጡረታ ፈንድን በኢንቨስትመንት ላይ በማዋል በትርፍ የሚገኘውን ገንዘብ ለማሳደግ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል፡፡

   የማህበራዊ ጥበቃ ሥርዓትን በመዘርጋትና አገልግሎቶችን በማስፋፋት የዜጎችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በትኩረት ይሰራል፡፡ በዚህም የማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞችን አስተማማኝና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የማህበራዊ ጥበቃ ፈንድ ጽ/ቤቶችን በማቋቋም የዜጎችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት እንዲያድግ ይደረጋል፡፡ ደሃና ተጋላጭ የሆኑ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋዊያን እንዲሁም ውሎና አዳራቸውን ጎዳና ላይ ያደረጉ የህብረተሰብ ክፍሎችን የልማታዊ ሴፍተኔት ፕሮግራም ተጠቃሚነት ለማሳደግ እንሰራለን፡፡

## 3.5 የባህል፣ ቱሪዝምና ስፖርት ልማትን ማረጋገጥ

1. ባህላዊ እና የተፈጥሮ ኃብቶቻችንንና መጠበቅና ማልማት ልዩ ትኩረት የምንሰጠው ይሆናል፡፡ ያሉንን ሀብቶች አሁን ካሉበት የህልውና ስጋት በመጠበቅ እና በመንከባከብ ለቀጣዩ ትውልድ ለማስተላለፍ የሚያስችሉ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ በማድረግ ባህላዊ እና ተፈጥሮ ሀብቶቻችን ለሀገራችን ለምጣኔ ሀብታዊ እና ማህበራዊ ልማት እንዲውሉ ለማድረግ እንሰራለን፡፡ ከዚህ አንፃር የባህል ልማት ስትራቴጂ፣ የቋንቋ ልማት ስትራቴጂ፣ የእደ ጥበብ ልማት ስትራቴጂ ወደ ተግባር እንዲቀየሩ እንሰራለን፡፡
2. ሀገራችን ያሏትን ዕምቅ ተፈትሮአዊ፣ ባህላዊ ሀብቶች በመጠቀም በቱሪዝም ዘርፍ ተወዳዳሪ በመሆን ማግኘት የሚገባትን ያህል ጥቅም ማግኘት አለመቻሏ እና ከአቻ ሀገራት አንፃርም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ መገኘቷን እንደሃገር የሚያስቆጭ ነው፡፡ በቀጣይ ዓመታት ያለንን ሀብት በሚመጥን መልኩ የቱሪዝምን ዘርፉን በማልማት ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነቱን ለማሳደግ የሚያስችል ስልት ቀይሰናል፡፡ ከዚህ አንጻር ከመዳረሻ ልማት፣ ገበያ እና ፕሮሞሽን፣ የቱሪዝም ምርት እና አገልግሎቶችን ዓይነት እና ጥራት ላይ ያተኮሩ ተግባራትን ትኩረት ተሰጥቶ ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል፡፡ የቱሪዝም ዘርፉን ለማጠናከር የሚረዱ ፖሊሲዎች፣ የሕግ ማዕቀፎች፣ የአሰራር ማስተካከያዎች የአደረጃጀት ለውጦች እንዲሁም የቴክኖሎጂ ግብዓቶችን በመፈተሽ በማስተካከልና በማዘጋጀት ተግባራዊ እንዲሆኑ የሚደረግ ይሆናል፡፡ የቅርስ ጥበቃና ልማት ፖሊሲ፣ የቱሪስት ደህንነትና ጥበቃ ስትራቴጂ፣ የመዳረሻ የቱሪዝም ምርት ልማትና አስተዳደር ስትራቴጂ፣ የገበያና ፕሮሞሽን ስትራቴጂ፣ የቱሪስት መረጃ ስርጭት ስትራቴጂ እና የመዳረሻ አካባቢ ማህበረሰብ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ስትራቴጂ ወደ ተሟላ ተግባራዊነት እንዲቀየሩ ይደረጋል፡፡
3. ሀገራችን ኢትዮጵያ በስፖርቱ ዘርፍ ዕምቅ አቅም ያላትና በርካታ ዓለምን ያስደመሙ ስፖርተኞች መፍለቂያ አገር ናት፡፡ ይሁንና አገራችን ያላትን እምቅ አቅም መጠቀም በሚያስችል መልኩ መስራት ባለመቻሉ በአካልና በአዕምሮ የዳበረ አምራች ዜጋ በመፍጠር ረገድ ክፍተቶች ተስተውለዋል፡፡ ይህንንም መሰረት በማድረግ ዜጎችን በስፋት በስፖርት ለማሳተፍ የሚስችሉ ምቹ ሁኔታዎች በመፍጠር ንቁና ጤናማ ዜጋ እንዲኖር የሚያስችሉ ተግባራትን ለማከናወን እንዲቻል እንሰራለን፡፡ የጸረ-አበረታች ቅመሞች ፖሊሲ ወደ ተግባር በማስገባት ከአበረታች ቅመሞች የጸዳ የስፖርት ማህበረሰብ ለመፍጠር እንሰራለን፡፡
4. በሀገራችን የአርትና መዝናኛ የፈጠራ ኢንዱስትሪው ለስራ እድል ፈጠራና ለሀገር ገቢ ማስገኘት ያለውን አስተዋጽኦ በመገንዘብ በተለይ ከቴክኖሎጂ እድገት ጋር ተያይዞ እየመጣ ያለውን ፍላጎት እድገት ታሳቢ በማድረግ ዘርፉ በእይታዊ፣ በትውና እና ስነ-ፅሁፍ ስራዎች በአለም ገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ስልቶችን በመቀየስ እንዲሁም የትወና ጥበባት ፖሊሲ ወደ ስራ በማስገባት የፈጠራ ኢንዱስትሪን በማጎልበት የምንሰራ ይሆናል፡፡

# ምዕራፍ አራት
# የሀገራችን ጥቅም ፣ የዜጎቻችንን ክብር የሚያስጠብቅ የውጭ ግንኙነት ተቋማትን መገንባት

**የአምስት ዓመት የፓርቲያችን የውጭ ግንኙነት ግቦች፤**

- ዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ እና የዲያፖራ ተሳትፎን ማጠናከር
- ጎረቤት ሀገር ተኮር ሆኖ ለትብብርና ለጋራ ተጠቃሚነት ትኩረት የሚሰጥ የዲፕሎማሲ ፖሊሲና ስትራቴጂ ማጠናከር
- ጠንካራ የውጭ ግንኙነት አስፈጻሚ ተቋማትን መገንባት

ብልፅግና የኢኮኖሚ ፍላጎት መሟላት ብቻ አይደለም፡፡ የዜጎች እና የሀገር ክብርን ይጨምራል፡፡ በመሆኑም ፓርቲያች የሚተገብረው የሀገራች የውጭ ግንኙነት ሁለቱንም መንትያ ግቦች የሚያሳካልን ይሆናል፡፡ በአንድ በኩል የሀገራችንን ኢኮኖሚያዊ ፍላጎት ሊያሟላ የሚችል እና ብሄራዊ ጥቅምን የሚያስከብር በሌላ በኩል ደግሞ ሀገራዊ ክብርን የሚያስጠብቅ ፤ የዜጎች መብት፤ ክብር እና ደህንነት የሚያረጋግጥ ይሆናል፡፡ ይህንን ሁለንተናዊ ብልፅግና የማሳካት ግንኙነት የረጅም ጊዜ ሉአላዊ ሀገርነትን፤ ነፃ የመንግስትነት ታሪክን፤ መቻቻል ያለበት ብዝሀነትን፤ መልካም መስተጋብሮች ፤ መወራረሶች አብሮነቶች ባለቤት ሀገር ውስጥ የፌደራሊዝም ጅማሮዎች መኖርን እንደ እሴት የሚያገናዝብ ነው፡፡ ፓርቲያችን የሚከተለው የውጭ ግንኙነት ከሀገር ውስጥ ጉዳያችን ያልተነጠለ እና ሀገራዊ ሁኔታችንን መነሻ የሚያደርግ እንዲሁም የውጭውን ከባቢ የሚያገናዝብ ነው፤፤ ሁለንተናዊ ብልፅግናን ለማረጋገጥ የሚያስችል የተመቻቸ ውጫዊ ሁኔታና ግንኙነት የሚፈጥር እንዲሆን ለማድረግ ፓርቲያችን አጠቃላይ እንቅስቃሴዎችን ያደርጋል፡፡

በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ቁጥር ከሶስት ሚሊዮን በላይ እንደሆነ ይገመታል ፡፡ ይሁን እንጂ ይህንን ሰፊ የህዝብ ቁጥር በአግባቡ የሚያስተናግድ የውጭ ግንኙነት ስራ በመስራት በኩል ውስንነቶች ነበሩ፡፡ አሁን ላይ ፓርቲያችን በሚከተለው ዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ ምክንያት ባለፉት ሁለት አመታት በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በሀገራቸው ያላቸው ሁለንተናዊ ተሳትፎ አድጓል፡፡

ፓርቲያችን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲውን ወደ ዜጋ ተኮር በመቀየር ቅድሚያ የዜጎቻችንን ደህንነት የሚያረጋግጥ እና ለጥቅሞቻቸው መከበር የሚቆም ሀገራዊ ጥቅማችንን የሚያስቀድም እና ለጎረቤት ሀገሮች ቅድሚያ የሚሰጥ ሀገራዊ ጥቅማችንን በዘላቂነት የሚያከብሩ እና በድንበር ተሻጋሪ ወንዞቻችን ፍትሀዊ ተጠቃሚነታችን የሚረጋገጥበት ዲፕሎማሲያዊ አቅጣጫ በልዩ ትኩረት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

## 4.1 ዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ እና የዲስፖራ ተሳትፎን ማጠናከር

1. ለስራ ወደ ውጭ የሚሄዱ ኢትዮጵያውያን በሚሄዱባቸው ሃገራት ሊገጥሟቸው የሚችሉ ፈተናዎችን ፣ መብትና ግዴታቸውን የተመለከቱ ቅድመ ዝግጅቶች እንዲያደርጉ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት በተለያዩ የዓለም ሃገራት የሚገኙ ሁሉም ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በሄዱበት እና በሚኖሩበት ሃገር ሁሉ ተገቢውን ሰብአዊ ክብርና ጥቅም እንዲያገኙ አበክሮ ይሰራል፡፡
2. በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ለሀገራችን ብልጽግና ፣ ለወንድሞቻቸው ደራሽ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ እንፈጥራለን፡፡ ዲያስፖራውን ማህበረሰብ በተለያዩ የቢዝነስ ዘርፎች በማሳተፍ ሃብት እንዲፈጥሩና ለዜጎች የስራ እድል እንዲያስገኙ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም የዳያስፖራ የውጭ ምንዛሪ የባንክ አካውንቶች በማስከፈት ገንዘብ እንዲቆጥቡ ያደርጋል፡፡
3. ከውጭ በሬሚንታስ የሚገባው ገንዘብ ህጋዊ ሂደት እንዲይዝ በማድረግ ፣ በዳያስፖራ ትረስት ፈንድ ድጋፍ የሚሰጡ የዳያስፖራ አባላትን ቁጥር በመጨመር እንዲሁም የህዳሴውን ግድብ ቦንድ ግዢ በዳያስፖራው ማህበረሰብ እንዲፈጸም በማድረግ ዲያስፖራው ለሀገራችን የሚኖረው አስተዋጽኦ እንዲያድግ ይደረጋል፡፡
4. ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በሄዱበት ሁሉ የሃገራቸውን ገጽታ በመገንባት ፣ ኢንቨስትመንትና ቱሪዝምን በመሳብ ፣ የሳይንስ እና የቴክኖሎጂ አማራጮችን ለሃገራቸው በማመቻቸት ፣ የልማት እና የፋይናንስ ምንጮችን በማፈላለግ እና በመሳሰሉት ጉዳዮች በመሰማራት የሃገራቸው ዲፕሎማት እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ እንፈጥራለን፡፡

## 4.2 ለትብብርና ለጋራ ተጠቃሚነት ትኩረት የሚሰጥ የዲፕሎማሲ ፖሊሲና ስትራቴጂ ማጠናከር

1. ከአለም አቀፍ እና ቀጠናዊ ድርጅቶች ጋር የሚኖረን ግንኙነት እንዲጠናከር በማድረግ የሃገራችንን የኢንቨስትመንት አማራጮች ፣ የወጪ እና ገቢ ንግድ ልውውጥ እንዲሰፋ ፣ የስራ እድል ፈጠራ እንዲጨምርና ዘላቂ የሃገራችን ልማት እንዲረጋገጥ እናደርጋለን፡፡ ኢትዮጵያ የአለም አቀፍ የንግድ አባል ለመሆን የጀመረችውን እቅድ ተገቢውን ድርድር በማቅረብ ፣ ለፖለቲካ አመራሩ ቅርብ ድጋፍ ፣ የአገራችንን ብሔራዊ ጥቅም ባስጠበቀ ሁኔታ እና በተቀናጀ አሰራር ከዳር ለማድረስ ይሰራል፡፡
2. የአፍሪካ ህብረት ሰላም እና ጸጥታ ለማስከበር በሚያደርገው እንቅስቃሴ ጠንካራ ተሳትፎ በማድረግ የሃገራችንን ተሰሚነትና ክብር እናሳድጋለን፡፡ የአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ የንግድ ቀጠና ወደ ተግባር እንዲገባ በማድረግ በአህጉሪቱ ውስጥ የሚካሄድ የወጪ እና ገቢ ንግድ ኢንዲስፋፋ፣ የጋራ ተጠቃሚነት እና የእርስ በእርስ ትስስር እንዲፈጠር እንሰራለን፡፡
3. የሀገራችን መልካም ገጽታን ለመገንባት ዋና ዋና የሃገር ውስጥ እና ዓለም አቀፍ የሚዲያ ተቋማት ፣ የቲንክ ታንክና አድቮኬሲ ተቋማት ፣ የምርምር ተቋማት ፣ ታዋቂ ምሁራንና ግለሰቦች ጋር በቅርበት በመስራት ፣ የሃገራችንን ወቅታዊና ተጨባጭ ሁኔታ እንዲገነዘቡ ማድረግ ፣ የሃገራችንን በጎ ገጽታ የሚያንጸባርቁ ዘገባዎችን ፣ ሪፖርቶችን ምስክርነቶችን እንዲሰጡ የማስቻል ፤ የዲጂታል ዲፕሎማሲ መሳሪያዎችን አጠቃቀም ማስፋት እንዲሁም የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ቡድን በተመረጡ ሃገራት ጉብኝት እንዲያካሂድ በማድረግ ፣ የሃገራችን ከተሞች እና ተቋማት ከሌሎች ሀገራት ከተሞች ፣ የምርምር ተቋማት ጋር ትስስርና ጓደኝነትን እንዲፈጥሩ ማድረግ ፣ የባህል ማዕከላትን በማስፋፋትና በማጎልበትና የባህል ማስተዋወቅ በማካሄድ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት በማጠናከር ሀገራዊ ገጽታችንን ማሻሻል በትኩረት የሚሰራበት ይሆናል፡፡
4. የቱሪዝም ገቢያችንን ለማሳደግ ይረዳ ዘንድ ከፍተኛ የቱሪስት አመንጪ በሆኑ ሃገራት በሃገራችን ያሉ የቱሪዝም አማራጮችን እናስተዋውቃለን፡፡ በተለያዩ ዓለም አቀፍ የቱሪዝም ትርዒቶች በመሳተፍ እና በማዘጋጀት ሃገራችን በቱር ኦፕሬተሮች ፓኬጅ እንድትካከት ይደረጋል፡፡ ከዚህ ሌላ ተከታታይነት ያላቸው ዓለም አቀፍ የቱሪዝም ኮንፈረንሶች በሃገራችን እንዲካሄዱ በማድረግ እና ቱሪስቶችን በመሳብ ሃገራችን ከዘርፉ የምታገኘው ምጣኔ ሃብታዊ ገቢ እናሳድጋለን፡፡

5. ከጎረቤት አገራት ጋር ያለንን ሁሉን አቀፍ ግንኙነት በማጠናከር ለሰላምና ጸጥታ ፣ለኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ትስስር ምቹ ሁኔታዎች ለመፍጠር በቀጠናው አገራት መካከል የጋራ ኮሚሽን ስብሰባዎች፣ የፖለቲካ ምክክሮች ፣ የጉብኝት ልውውጦች እና ፎረሞች በመጠቀም የጋራ ፕሮጀክቶች እንዲነደፉ እና ተግባራዊ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ የተከለሉ ድንበሮች ማስተዳደር፣ ያልተከለሉት ስለሚካለሉበት ሁኔታ ማመቻቸት፣ በድንበር አካባቢ የሚከሰቱ ግጭቶችን እና ህገ-ወጥ ተግባራትን ማስወገድ በተጨማሪም የድንበር ተሻጋሪ ሀብቶቻችን ፍትሃዊ አጠቃቀም ለማስፈንና የጋራ ተጠቃሚነት ለማሳደግ ድርድሮችን የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም በሚያስከብር መልኩ ማካሄድ፣ የናይል ውሃ አጠቃቀም የትብብር ማእቀፍ ያልፈረሙ ሀገራት እንዲፈርሙ ማድረግ እና ያላጸደቁት እንዲያጸድቁ ማግባባት በጎረቤት ሃገራት ዲፕሎማሲያችን ትኩረት የምንሰጠው ጉዳይ ይሆናል፡፡

## 4.3 ጠንካራ ውጭ ግንኙነት አስፈጻሚ ተቋማትን መገንባት

1. በዲፕሎማሲ መስክ ብቃት ያላቸው አመራሮችን ለማፍራት የውጭ ግንኙነት ማሰልጠኛ ተቋም የስልጠና እና የምርምር ልህቀት ማዕከል እንዲሆኑ በማድረግ ብቁ ዲፕሎማቶችን ያፈራሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የህግ ማእቀፎችን እና አሰራሮች እንዲሻሻሉ በማድረግ፣ ሁሉም አገልግሎቶችን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በማስደገፍ፣ የክትትል እና የግምገማ ስርዓት በማጠናከር እንዲሁም የመልካም አስተዳደር ስራዎችን በማስፈን ሃገራዊ ብልጽግናችን እውን ለማድረግ አጋዥ ይሆናሉ፡፡
2. የሃገር ፍቅር ስሜታቸው የጎላ፣ በዲፕሎማሲ አቅማቸው የበቁ፣ በትምህርት እና በልምድ የዳበሩ እንዲሁም ህዝባዊ ቅቡልነትና ግለሰባዊ እውቅና ያላቸው ዜጎችን በአንባሳደርነትና በዲፕሎማትነት በተለያዩ ሃገራት በመመደብ የሃገራቸውን ገጽታ በመገንባት፣ የሁለትዮሽ ማህበራዊ መስተጋብሮችን በማሳደግ፣ የቱሪዝምና የኢንቨስትመንት አማራጮችን ለሃገራችው በመሳብ ሃገራዊ ብልጽግናችን እውን እንዲሆን ይሰራል፡፡

በተግባር የተፈተን ዕቅድ ያዘጋጀውን፣ግልፅ ርዕይ የሰነቀውን፤ለዘመናት ያሡሩንን ማነቆዎች የመበጣጣሽ ዘዴ የያዘውን የተስፋችንን መዳረሻ እውነት የጨበጠውን ብልፅግና ይምረጡ፣